# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 161 የካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# «ኢትዮጵያ በበጋ ስንዴና በአረንጓዴ ዐሻራ የሠራችው ውጤታማ ሥራ ለአፍሪካ ተሞክሮ የሚሆን ነው»

- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም በአረንጓዴ ዐሻራና በበጋ ስንዴ የሠራችው ውጤታማ ሥራ ለአፍሪካ ተሞክሮ እንደሚሆን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ አስታወቁ።

ከ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን ኢትዮጵያ ያዘጋጀችው ከፍተኛ የግብርና የውይይት መድረክ «አፍሪካ በምግብ ራሷን ትችላለች» በሚል መሪ ሃሳብ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ትናንት ተካሂዷል።

በወቅቱ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለመቋቋም የአረጓዴ ዐሻራንና የበጋ ስንዴን ልማትን ተግባራዊ በማድረጓ ተጨባጭ ውጤት አስመዝግባለች። ይህም አፍሪካ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ለምትሠራው ሥራ ተሞክሮና ምሳሌ የሚሆን ነው።

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ተከታታይ ዓመታት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብርን ተግባራዊ በማድረጓ የአየር ንብረት ለውጥ የደቀነውን አደጋ ከመከላከል ባሻገር ምርትና ምርታማነት አሳድጋለች ብለዋል።

በተለይ በበጋ ስንዴ የራሷን የስንዴ ፍጆታ ከማሟላት ባሻገር ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሏን ጠቅሰው፤ በአረንጓዴ

«ኢትዮጵያ በበጋ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









## አፍሪካ የተሻለ የጤና አገልግሎት አማራጭ እንዲኖራት ኅብረቱና አባል ሀገራቱ በትኩረት ሊሠሩ ይገባል

- 60 በመቶ የሚሆነውን ክትባት በአፍሪካ ማምረት የሚያስችል ፕሮግራም ተቀርጿል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ የተሻለ የጤና አገልግሎት አማራጭ እንዲኖራት ኅብረቱና አባል ሀገራቱ በትኩረት ሊሠሩ ይገባል ሲሉ የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል (ሲዲሲ) ዋና ዳይሬክተር ጃን ካሴያ (ዶ/ር) ገለጹ። 60 በመቶ የሚሆነውን ክትባት እ.አ.አ በ2040 በአፍሪካ ማምረት የሚያስችል ፕሮግራም መቀረጹ ተመላክቷል።

ከ37ኛው መደበኛ የመሪዎች ስብሰባ ጎን ለጎን የሲዲሲ አፍሪካ ዋና ዳይሬክተር ጃን ካሴያ (ዶ/ር) በአህጉሪቱ ያለውን የኅብረተሰብ ጤና አገልግሎት እና

አፍሪካ የተሻለ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ጃን ካሴያ (ዶ/ር)

## ከኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ

## በተጓዳኝ የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ግንኙነት የሚያጠናክሩ ሥራዎች ተከናውነዋል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁና የዲፕሎማሲ ግንኙነትን የሚያጠናክሩ ሥራዎች መከናወናቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር) ከኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ በተጓዳኝ በኢትዮጵያ በኩል የተከናወኑ ዋና ዋና ሥራዎችን በሚመለከት መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸውም ከአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቁና የዲፕሎማሲ ግንኙነት የሚያጠናክሩ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከበርካታ

ከህብረቱ የመሪዎች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር መለስ ዓለም (ዶ/ር)






## የእንስሳት ሀብት ልማቱ ተስፋና ፈተናዎች

**ተስፋ ፈሩ**

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከአፍሪካ አንደኛ፣ ከዓለም አምስተኛ መሆኗ ተደጋግሞ ይነገራል፡፡ ለመሆኑ ሀገራችን ይህን ሀብቷን ምን ያህል እየተጠቀመችበት ነው?

በእንስሳት ሀብት ፖሊሲና በመዋቅራዊ ሂደቱ ላይ ትኩረት ያደረገ ጥናት ያካሄዱት የእንስሳት ፖሊሲ ጥናት ተመራማሪው ደሳለኝ ቤኛ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ የኢትዮጵያ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እያደገ

የእንስሳት ሀብት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## «የአህጉሪቱን ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት የወጣቱን አቅም መጠቀም የሚያስችል ማሻሻያ ማድረግ ይገባል»

- ቺዶ ምፔምባ በአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ወጣቶች ልዩ መልዕክተኛ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የአህጉሪቱን ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት የወጣቱን አቅም መጠቀም የሚያስችል በፖሊሲ የተደገፈ ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል ሲሉ በአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ወጣቶች ልዩ መልዕክተኛ ቺዶ ምፔምባ ገለጹ።

የአፍሪካ ኅብረት የአፍሪካ ወጣቶች ልዩ መልዕከተኛ ቺዶ ምፔምባ የወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራን አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፤ የአህጉሪቱን ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት የወጣቱን እምቅ አቅም መጠቀም ይገባል።

በአፍሪካ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ወጣቶችን በዘላቂ የልማት ግቦች እና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ውስጥ ማሳተፍ እንደሚገባ ገልጸው፤ የወጣቱን እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ለማዋል መንግሥታት በፖሊሲ የተደገፈ ተቋማዊ አሠራሮች እና ማሻሻያዎችን ማድረግ እንደሚገባቸው አስታውቀዋል።

የወጣቱ ኃይል የአህጉሪቱን የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዘርፍ በአዲስ ዕይታ የማሸጋገር አቅም አለው ያሉት ልዩ መልዕክተኛዋ፤ በአህጉሪቱ የሚታየውን ሰፊ የወጣቶች ሥራ አጥነት ለመቅረፍ ወጣቶችን ማስተማርና ማሰልጠን ላይ ትኩረት ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

የአህጉሪቱ ወጣቶች በሥራ ፈጠራ እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ እንዲሳተፉ ድጋፍና ክትትል ከማድረግ ባለፈም የወጣቱን ሰፊ እምቅ አቅም ጥቅም ላይ ለማዋል መንግሥታት በፖሊሲ የተደገፈ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በአፍሪካ የተያዘውን የአጀንዳ 2063 ዕቅድ ለማሳካት 62 በመቶ በላይ የሚሆኑት የአህጉሪቱ ወጣቶች ሚና ሰፊ ድርሻ ያለው በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ በማሳተፍ ተጠቃሚ መሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

የአፍሪካ ወጣት ትልቁ ፈተና ዛሬም ሥራ አጥነት በመሆኑ ኅብረቱም ሆነ አባል ሀገራቱ በአህጉሪቱ በሚገኙት የወጣቶች ቁጥር የሚመጣጠን የሥራ ዕድል ለማመቻቸት በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

በአፍሪካ ያለው የሥራ ዕድል ፈጠራ ከሕዝብ ብዛቱ ጋር አብሮ የሚያድግ ሊሆን እንደሚገባ አመላክተው፤ በዚህም የትምህርት አድማሱን እና የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ማስፋፋት እንደሚገባ ተናግረዋል።

37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ «ለ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን አፍሪካዊ ማስተማር፤ የማይበገሩ የትምህርት ሥርዓቶች በመገንባት በአፍሪካ ሁሉን አቀፍ፣ የሕይወት ዘመን፣ ጥራትና አግባብነት ያለው የትምህርት ተደራሽነትን ማስፋት» በሚል መሪ ሃሳብ ተካሂዷል።

# በክልሉ ለመጽሐፍት ህትመት የሚውል 220 ሚሊዮን ብር ተሰበሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ለአንደኛ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍት ህትመት የሚውል 220 ሚሊዮን ብር ከኅብረተሰቡ መሰብሰቡን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድርና የክልሉ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አንተነህ ፍቃዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በክልሉ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መማሪያ መጽሐፍት ህትመት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

በዘንድሮ ዓመት ለሚማሩ ተማሪዎች አንድ መጽሐፍ ለአራት ተማሪዎች ለማዳረስ እየተሠራ ነው መሆኑን አቶ አንተነህ ገልጸዋል፡፡

ለመጽሐፍት ህትመቱ በአጠቃላይ ከኅብረተሰቡ ለመሰብሰብ የታቀደው 600 ሚሊዮን ብር መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

የመጽሐፍ ህትመቱ ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ በክልሉ መንግሥት አቅም ማሳተም የሚቻል አለመሆኑን ጠቅሰው፤ የህትመቱን የተወሰነ ወጪ በኅብረተሰብ መዋጮ ለመሸፈን የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነውም ብለዋል፡፡

በዚህም በክልሉ የአንደኛ ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ህትመት የሚውል 220 ሚሊዮን ብር ከኅብረተሰቡ መሰብሰቡን ነው የተናገሩት፡፡

በክልሉ በጉራጌ፣ በምሥራቅ ጉራጌና በስልጤ ዞኖች እስካሁን 29 ሚሊዮን ብር በሚጠጋ ሀብት ተሰብስቦ የ77 ሺህ 382 መጽሐፍት ህትመት መከናወኑን የገለጹት አቶ አንተነህ፤ መጽሐፍቱ ታትመው መሰራጨታቸውን ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ዞኖችም በቅርቡ መማሪያ መጽሐፍቱን ወደ ማሳተም ሥራ ይገባሉ ሲሉ አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ አንተነህ ገለጻ፤ በክልሉ የሚገኙ ባለሀብቶች፣ የአካባቢው ተወላጆች፣ የተማሪ ወላጆች እንዲሁም የተለያዩ ኅብረተሰብ ክፍሎች በጋራ በመሆን የመማሪያ መጽሐፍቱን አሳትመው ለትምህርት ቤቶች



አቶ አንተነህ ፍቃዱ

እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ሀብት የማሰባሰብ ሥራው ተጠናክሮ የሚቀጥል ነው፡፡

በክልሉ ከመንግሥት መዋቅሮች ለመጽሐፍት ህትመቱ በጀት መድበው እየሠሩ የሚገኙ መኖራቸውን የተናገሩት ኃላፊው፤ በስልጤ ዞን የወራቤ ከተማ አስተዳደር ለመጽሐፍት ህትመቱ በጀት መድቦ በመሥራት ለአብነት የሚጠቀስ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የትምህርት ዘርፉን ከገባበት ችግር ለማውጣት የኅብረተሰቡን ተሳትፎ የሚጠይቅ እንደሆነም ነው አቶ አንተነህ የጠቆሙት፡፡

የመማሪያ መጽሐፍቱ ታትመው እስኪጠናቀቁ ድረስ የመጽሐፍቱ ቅጂ ተሠራጭቶ ጊዜያዊ መፍትሔ መሰጠቱን የገለጹት አቶ አንተነህ፤ በ2015 ዓ.ም በክልሉ ላሉ ተማሪዎች አንድ ለአምስት የሚዳረስ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መጽሐፍ መታተሙን አስታውሰዋል፡፡

በቂ የትምህርት ግብዓት አቅርቦት ያለመኖርና ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶች ቁጥር አነስተኛ መሆን ለዘርፉ ዕድገት ማነቆ መሆናቸውን አቶ አንተነህ ገልጸዋል።

# በዞኑ ከ150 በላይ ቀበሌዎች

## አስተማማኝ ሰላም አግኝተዋል

**ውብሸት ሰንደቁ**


ሶዶ፡- በወላይታ ዞን 153 የወንጀል ስጋት የነበረባቸው ቀበሌዎች ተለይተው በተሠሩ የሕዝብን ሰላምና ደህንነት የማረጋገጥ ሥራዎች ቀበሌዎቹን ከአንፃራዊ ሰላም ወደ አስተማማኝ ሰላም ማሸጋገር ተችሏል ሲል የዞኑ አስተዳደር ገለጸ።

የወላይታ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሳሙኤል ፎላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕዝብ ደህንነት የማስጠበቅ ጉዳይ ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በዞኑ ከዚህ በፊት 153 ቀበሌዎች የስጋት ቀጣና ሆነው እና ተለይተው ሲሠራባቸው ቆይቷል። በዚህም ሁሉን ቀበሌዎች ከአንፃራዊ ሰላም ወደ አስተማማኝ ሰላም ማሸጋገር ተችሏል።

ነፃ የተደረጉት ቀበሌዎች የወንጀል ስጋት የነበረባቸው መሆኑን ገልጸው፤ በቀበሌዎቹ ዝርፊያ እና ንጥቂያ እንዲሁም በሌሎች ወንጀሎች የሚጠረጠሩ ግለሰቦች የነበሩባቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

በተያዘው ዓመት የሕዝብ ደህንነት እና ሰላም የስድስት ወራት አፈፃፀም በተለያየ ደረጃ መገምገሙን አስረድተው፤ በዚህም ወላይታ ከስጋት ነፃ የሆነ ዞን ማድረግ መቻሉን አረጋግጠናል ሲሉ ተናግረዋል። በዞኑ አንፃራዊ ሳይሆን አስተማማኝ ሰላም ለማረጋገጥ የተሠራው ሥራ ውጤታማ ሆኗል ሲሉም ገልጸዋል።

የተሠራው ሥራ ለሀገር ትልቅ ተሞክሮ ሊሆን



አቶ ሳሙኤል ፎላ

የሚችል ነው ያሉት አቶ ሳሙኤል፤ የፌዴራል እና የክልል የፀጥታ አካላትም ከዞኑ የሰላም እና ደህንነት ሥራዎች ተሞክሮ መውሰዳቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ሳሙኤል ገለፃ፤ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታም ከየትኛውም አካባቢ ማንም በነፃነት የሚንቀሳቀስበት የሰላም ተምሳሌት ዞን ሆኗል። በዞኑ አልፎ አልፎ የሚታዩ ወንጀሎች መደበኛ ወንጀሎች ናቸው።

በዞኑ ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት ከሀገራዊ ጥያቄ ጋር ተያይዞ የአሁኑን መሰል ሰላም እንዳልነበረ እና ከፍተኛ ስጋት ከነበሩባቸው መካከል ተጠቃሽ እንደነበረ ጠቁመዋል።

የሕዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት የሚረጋገጠው መጀመሪያ ሰላም ሲኖር እና የሕዝብ ደህንነት ሲጠበቅ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ ይህን መነሻ በማድረግ በተሠራው ሥራ ውጤት ተገኝቷል። ቀሪ ሥራዎችም እየተሠሩ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል።

የፀጥታ ተቋማት ማለትም ከፖሊስና ከሚሊሻ እንዲሁም ከአጠቃላይ ከሕዝቡ ጋር ሕዝቡን የሰላም ባለቤት እንዲሆን ለማስቻል ውይይቶች ተካሂደው የተሠራ መሆኑ ለውጤታማነቱ እንዳገዘ ተናግረዋል። የሀገር ሽማግሌዎች እና የሃይማኖት ተቋማት ጋርም ተመሳሳይ ውይይቶች መካሄዳቸውን አብራርተዋል።

በዞኑ የኑሮ ውድነት፣ ሥራ አጥነት፣ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንም አያይዘው ተናግረዋል።

ዜና

# ቀይ መስቀል
## ከሦስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ድጋፍ አድርጓል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ስድስት ወራት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚገኙ ከሦስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የተለያየ ድጋፎች ማድረጉን የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር አስታወቀ፡፡

የማኅበሩ ምክትል ዋና ጸሐፊ አበራ ሉሌሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቀይ መስቀል ባለፉት ስድስት ወራት በአጠቃላይ ሦስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ለሚሆን ሰው የተለያዩ ድጋፎችን አቅርቧል።

በ2016 በጀት ዓመት በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው እንዲሁም በተለያዩ ግጭቶች ከአካባቢያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች የምግብ፣ የቁሳቁስ፣ የብር፣ መድኃኒትና የአምቡላስ ድጋፎችን እንዲሁም ለአደጋ ቅነሳ የሚያግዙ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን አከናውኗል ብለዋል።

ጤና ላይ መድኃኒት ከማቅረብ በተጨማሪም ለጤና መሠረት የሆኑ እንደ መጠጥ ውሃ ቁፋሮና የመጸዳጃ ቤት ግንባታዎችን በማከናወን እንዲሁም የተለያዩ ወረርሽኝ በሚያጋጥሙባቸው አካባቢዎች ስለ በሽታው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሠራቱን አብራርተዋል፡፡

በስድስት ወራት ውስጥ የተከናወኑ ድጋፎችን ለማቅረብ ከ555 ሚሊዮን 337 ሺህ ብር በላይ ወጪ መደረጉን አስታውቀው፤ ከዚህ ውስጥ 410 ሚሊዮን ብሩ ለ736 ሺህ 808 ሰዎች ተደራሽ የሆኑበት የመድኃኒትና የጤና አገልግሎት፣ የአምቡላንስ አገልግሎት ፣ የምግብ ድጋፍ እንዲሁም በግጭት ምክንያት የተጎዱ ሰዎችን ለመርዳት ወጪ የተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ማኅበሩ በርካታ ሥራዎቹን በበጎ ፍቃደኛ ሰዎች አማካኝነት የሚያከናውን ሲሆን ይህም የሚያወጣውን ወጪ በመቀነስ ከፍተኛ ድጋፍ እንዳደረገለት አቶ አበራ ተናግረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ማኅበሩ 200 ሺህ በጎ ፍቃደኞች እንዳሉት ጠቁመው፤ ከነዚህ ውስጥ 140 ሺ የሚሆኑት ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አቶ አበራ እንዳመላከቱት፤ በኢትዮጵያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ሰብዓዊ ርዳታ ስለሚያስፈልጋቸው ማኅበሩ ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ በሚያገኘው ድጋፍ ርዳታዎችን ተደራሽ ለማድረግ እየሠራ ይገኛል።

ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ሰብዓዊ ድጋፎችን ተደራሽ ለማድረግ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ የማኅበሩ ሠራተኞች የተለያዩ ጉዳቶች እየደረሰባቸው መሆኑን ያስታወሱት አቶ አበራ፤ ጉዳት የሚያደርሱ አካላት ቀይ መስቀል ለሁሉም የሰው ልጆች ርዳታ ለማቅረብ የሚንቀሳቀስ መሆኑን በመረዳት ተገቢውን ድጋፍና ጥበቃ ሊያደርጉ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ላለፉት 80 ዓመታት በሁሉም ሀገሪቱ ክፍሎች በመንቀሳቀስ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ሲያግዝ መቆየቱን አስታውሰዋል።



## በባቱ ከተማ የመንገድ ላይ የደህንነት ካሜራዎች እየተገጠሙ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

ባቱ፡- በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን ባቱ ከተማ የመንገድ ላይ የደህንነት ካሜራዎች እየተገጠመ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ አህመዲን እስማኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የባቱ ከተማ እያደገችና እየሰፋች መሆኗን ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶችን ለመከላከል የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው።

የባቱ ከተማን ደህንነት ለማስጠበቅ በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራ መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ ዘመናዊ አሠራሮች እየተተገበሩ መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባ አህመዲን፤ በጸጥታ አካላት በመታገዝ የኅብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ እንዲሁም የከተማዋን ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማረጋገጥ የተለያዩ የደህንነት ካሜራዎች በከተማዋ እየተገጠሙ መሆኑን ተናግረዋል።

አሁን ላይ የሲሲ ሲቪ ካሜራ ገጠማ በመጠናቀቁ በከተማዋ መግቢያ በር ላይ አዳዲስና ዘመናዊ የመንገድ ላይ የደህንነት ካሜራ መግጠም ተጀምሯል ያሉት ከንቲባ አህመዲን፤ ይህም ሕዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ፣ ሐይቅ ዳርቻ ላይ እና ሌሎች አካባቢዎች ላይ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የከተማዋ መግቢያ ላይ የተገጠመው የመንገድ የደህንነት ካሜራ አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ የገለጹት ከንቲባ አህመዲን፤ የሚገጠሙት የደህንነት ካሜራዎችም ወንጀልን ቀድሞ በመከላከል ዜጎች ደህንነት ተሰምቷቸው እንዲኖሩ የሚያስችሉ መሆናቸውም ገልጸዋል።

እንደ ከንቲባ አህመዲን ገለፃ፤ መጀመሪያ እንደ ከተማ አስተዳደር እቅድ የተያዘው የመንግሥት አገልግሎት በሚሰጥባቸው ተቋማትና ጽሕፈት ቤቶች ላይ የሲሲ ቲቪ ካሜራ የመግጠም ሥራ ነበር። ይህም 25 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እንቅስቃሴ መቆጣጠር አስችሏል። ይህም ሥራ ሲጠናቀቅ የመንገድ ላይ የደህንነት ካሜራዎች ገጠማ ተጀምሯል ብለዋል።

በቀጣይም በከተማዋ የተለያዩ ጎዳናዎች ካሜራዎችን የመትከል እቅድ መኖሩን የጠቀሱት ከንቲባ አህመዲን፤ የደህንነት ካሜራ አገልግሎት የብዙ ተቋማትን ቅንጅትና በርካታ መዋለንዋይ እንደሚፈልግ ተናግረዋል። የካሜራዎቹ ቀረፃና የቁጥጥር ሥራውም ያለምንም መቆራረጥ እንዲሠራ ይደረጋል ብለዋል።

## አውደ ርዕዩ ወጣቱ ትውልድ ለሀገር ማበርከት ያለበትን አስተዋጽዖ ያሳያል

ሳሙኤል ወንደሰን



ኢንጂነር ዘለቀ ረዳ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ ወጣቱ ትውልድ ለሀገሩ ማበርከት ያለበትን አስተዋጽዖ በሚያሳይ መልኩ መዘጋጀቱን ኢንጂነር ዘለቀ ረዳ (ዶ/ር) ተናገሩ።

«ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን» በሚል መሪ ሃሳብ እየታየ ያለው የዲፕሎማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እየተጎበኘ ይገኛል።

በሳይንስ ሙዚየም ተገኝተው የፎቶ አውደ ርዕዩን የጎበኙት የቀድሞ የኅብር ፓርቲ አመራር ኢንጂነር ዘለቀ ረዳ (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት። አውደ ርዕዩም ይህችን ታላቅ ሀገር በሚመጥን መልኩ የተዘጋጀ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊመለከተው ይገባል ብለዋል።

አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት ደረጃ ለመድረስ የተከፈለውን ዋጋ ያሳያል ያሉት ኢንጂነር ዘለቀ፤ ይህንን ዋጋ ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ወጣቱ ሀገሩን ማወቅ አለበት። ይህም አውደ ርዕይ ወጣቱ ትውልድ ስለሀገሩ እንዲያውቅ እና ለሀገር ማበርከት ያለበትን አስተዋጽዖ እንዲገነዘብ ያደርጋል ብለዋል።

ኢንጂነር ዘለቀ እንዳሉት፤ አውደ ርዕዩ የሕዝብን ጉዳይ ለሕዝብ ለማሳወቅ በነፃ ኅብረተሰቡ እንዲጎበኝ ተደርጓል። ይህንን ዕድል በመጠቀም ኢትዮጵያን ማወቅ ያስፈልጋል። ሀገር እየሠራች ያለውን በሌላ አንፃር ደግሞ እኛ ከሀገር የምንጠብቀው እንዲሳካ በጋር መተባበርና መሥራት ይገባል ነው ያሉት።

አሁን ያለው ሕዝብ ከማወቅ ይልቅ በግምት የሚናገረው ይበዛል። አውደ ርዕዩ ሕዝብ ከግምት ፖለቲካና አስተሳሰብ እንዲወጣ በማድረግ ስለሀገሩ ግንዛቤ ይሰጣል ያሉት ኢንጂነር ዘለቀ፤ ወጣቱ የነገ ሀገር ተረካቢ እንደመሆኑ መጠን ሀገሩን ማወቅ አለበት። ስለዚህ አውደ ርዕዩ በስፋት እንዲጎበኝ እና ወጣቱ ሀገሩን እንዲረዳ ማድረግ ላይ መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ይህችን ሀገር እዚህ ለማድረስ የተከፈለው ዋጋ ብዙ ነው። ከዓድዋ በኋላ በዲፕሎማሲ የተከናወኑ በርካታ ዓድዋዎች አሉ። በአውደ ርዕዩ የተገነዘብኩትም ይህንን ነው ያሉት ኢንጂነር ዘለቀ፤ ቀደምት አባቶች ኢትዮጵያዊ ያደረጋቸው ምን እንደሆነ በመለየት ከመገፋፋት ፖለቲካ መውጣት ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በትምህርት ቤት እንዲሰጥ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም ትውልዱ በትንሹ ብዙ ነገር ማወቅ የሚችል ነው ያሉት ኢንጂነር ዘለቀ፤ የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲ የሚገልጽ መጽሐፍ በውጭ ጉዳይ መዘጋጀቱ የሚደነቅ መሆኑንም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሀገራዊ ምክክሩ ስኬታማነት ሁሉም የዜግነት ግዴታውን ሊወጣ ይገባል!

ኢትዮጵያ በረጅም ዘመናት የታሪክ ጉዞዋ ጥሩም ሆነ መጥፎ ታሪኮችን አሳልፋለች፡፡ የነጻነትና የአይበገሬነት ተምሳሌት የመሆኗን ያህል በጦርነት፤ በርሃብ፤ በዜጎች መፈናቀልና የጥላቻ ትርክት አላስፈላጊ ዋጋዎችንም ከፍላለች፡፡

አብዛኛውን የኢትዮጵያን የውስጥ ታሪክ መለስ ብሎ ላየው የውስጥ አለመግባባት፤ግጭትና ጦርነት የበዛበት ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ መግባባት ካለመቻላችንም በላይ የግጭትና የጦርነት መንስኤ እስከ መሆን ደርሷል፡፡

ይህ ደግሞ ሀገሪቱን በማያባራ ግጭትና ጦርነት ውስጥ ከቷል፤ ለበርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ኪሳራም ዳርጓል፡፡ ለሀገሪቱ ዕድገትም ፈተና ሆኗል፡፡ በአንድ ሀገር ላይ ቆመን የጋራ አሰባሳቢ ትርክት መገንባት አቅቶንም ረጅም ዘመን አሳልፈናል፡፡ ትናንትናችን የአሁንና የነገ ተግዳሮታችን ሆኖ ኖሯልም፡፡

ይህ የታሪካችን ጠባሳ ግን አንድ ቦታ መቆም አለበት ተብሎ እንቅስቃሴ ከተጀመረም ዋል አደር ብሏል፡፡ የግጭት፣የጦርነት፣ያለመግባባት ታሪካችን ተዘግቶ በጋራ ታሪኮቻችን ላይ የምንግባባ፤ ለጋራ ሀገራችን የምንተጋ፤ ለልጆቻችንም የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማውረስ የጋራ ዕሳቤ የጨበጥን አዲስ ትውልድ መሆን ይገባናል በሚል እሳቤ እንደሀገር የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ከገባን ሁለት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡

በእነዚህ ጊዜያትም ምክክሩ የሚመራበትን አቅጣጫ ከመቀየስ ጀምሮ የሌሎችን ሀገራት ተሞክሮዎችን የመቀመርና በምክክሩ የሚሳተፉ ዜጎችን የመለየት ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ በቀጣይም የምክክሩን አጀንዳዎችን ከኅብረተሰቡ የመቀበልና ምክክሩን ወደ መሬት የማውረድ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ስለሆነም ሀገራዊ ምክክሩ የቀድሞ ችግሮቻችን፤ አሁን ያሉት ችግሮቻችን መፍቻና በቀጣይም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳያጋጥሙን የመፍትሄ አቅጣጫን የሚጠቁመን መድህን መሆኑን አምኖ ለተግባራዊነቱ በቁርጠኝነት መታገል ይጠበቅብናል፡፡ በሀገሪቱም መተማመን የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት ለመመስረትም እርሾ ሆኖ እንደሚያግዝ እምነት መጣል አለብን፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ በመሠረታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መግባባት እንዲኖር ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ሁሉም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ሲችል ነው፡፡ የምክክር ሂደቱ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ተሳትፎ የሚጠይቅና ውጤታማነቱም በእያንዳንዳችን አበርክቶ ላይ የሚወሰን ነውና፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ በቅድሚያ ሁሉም ነገር በንግግር እና በምክክር ይፈታል የሚል እምነት መጨበጥና ይህኑ ባህል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ዘመናትን የተሻገሩ ጥያቄዎችም ሆኑ እነሱን ተከትለው የመጡ አለመግባባቶች በምክክር እና በውይይት እንደሚፈቱ አምኖ መስራት ዘመኑ የሚጠይቀው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

የወሰንም ሆነ የማንነት ጥያቄ እንዲሁም ራስን በራስ ማስተዳደር እና የፍትህ ጥያቄዎች በአጠቃላይ የፖለቲካ ጥያቄዎች እና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች በሙሉ በሀገራዊ ምክክር ሊፈቱ የማይችሉበት ምክንያት አይኖርም፡፡

አሁን ያሉት አለመግባባቶች ተወግደው በፍቃደኝነት እና በመግባባት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ምክክሩ የማይተካ ሚና አለው፡፡ ሀገራዊ ምክክሩ ከዘመን ወደ ዘመን ሲንከባለሉ የመጡ ችግሮችን ለመፍታትና የመወያየትና የመነጋገር ባህልንም ለማዳበር ይረዳል፡፡ በመወቃቀስ ላይ የሚያተኩረውንም የፖለቲካ ባህላችንንም ወደ መነጋገር፤ መተባበርና መደጋገፍ እንዲመጣ ያደርጋል፡፡

ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን በርካታ ችግሮችን አስከትሎብናል፡፡ ከመነጋገር ይልቅ በር ዘግቶ መወቃቀስና አልፎ ተርፎም ነፍጥ እስከ ማንሳትና መገዳደል ድረስ አድርሶናል፡፡ አሁን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ግጭት፤ ጦርነትና መወነጃጀል ሳይሆን ውይይትና ምክክር ብቻ ነው፡፡

ስለዚህም ችግሮችን በውይይት የመፍታት ባህልም እንደሀገር ሊጎለብት ይገባል፡፡ የስልጣኔም አንዱ መለኪያም ይኸው ነውና፡፡ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ሥራ ውስጥም ሆነ በሌሎች መስኮች የተሰማሩ ወገኖች፣ ለውይይት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፡፡ ሀገራዊ ምክክሩን እንደ ዕድል ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

እንደ ሕዝብም የታሪካችን አንዱ ክፋይ ሆኖ ዘመናትን የተሻገረውን ጦርነትና ግጭትን ለማስወገድና የተረጋጋች፤ ሰላሟ የተጠበቀ እና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመጪው ትውልድ ለማውረስ ሀገራዊ ምክክሩ ይዞ የመጣውን ዕድል መጠቀም ሀገርን የማሻገር አንዱ ተልዕኮ ነው፡፡

ስለዚህም በየትኛውም ጫፍ ያለ ኢትዮጵያዊ በዚህ የምክክር ሂደት መሳተፍና የመፍትሄው አካል መሆን ሀገርን ማዳን መሆኑን ሊረዳ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ</u>
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ጥራት ያለው ባለሙያ ለማፍራት.....

ጋሹ ይግዛው (ከወሉ ሰፈር)

ትምህርት የሁሉም ሙያዎች መሠረት ነው ። በትምህርት ጥራት ላይ የሚሰራ ሥራ የሌሎችን የሙያ መስኮች ጥራት ማስጠበቅ የሚያስችል ነው። ለትምህርትና ሙያ ጥራት መምጣት ደግሞ ፈተና አንዱ አማራጭ ነው፤ ብቸኛው ነው ብሎ ማሰብ ግን የዋህነት ይመስለኛል።

በትምህርት ጥራት ላይ በትብብር መሥራት ካልተቻለ የሌሎችን የሙያ ዘርፎች ጥራት ማምጣትም፤ በእውቀትና በክህሎት የሚሠራ ብቁ ባለሙያ ማግኘትም "ልፋ ያለው በህልሙ አቅማዳ ይሸከማል" ካልሆነ በስተቀር ፋይዳ የለውም። ለሌላ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ መነሻ ሊሆን እንደሚችልም ማሰብ ተገቢ ነው ።

የትምህርት ጥራት ችግር ውስጥ ሊወድቅ የሚችለው ድንገተኛ በሆነ ክስተት ሳይሆን፤ በረጅም ዓመታት ሲንከባለሉና ትኩረት በተነፈጉ ችግሮች ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። ከቅድመ መደበኛ ትምህርት እስከ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ያለውን የመማር ማስተማር ሥርዓት መፈተሽና አስፈላጊውን እርምት በየደረጃ መውሰድን የሚጠይቅ ነው።

የትምህርት ጥራት በትምህርት ሚኒስቴር፣ በየክልሉ ትምህርት ቢሮዎች፣ በየዞን ትምህርት መምሪያዎች፣ በየወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤቶች ባሉ የትምህርት ባለሙያዎችና በመምህራን በሚሠሩት ሥራ ብቻ ማምጣት ይቻላል ብሎ ማሰብ ተገቢ አይደለም በመንግሥት ጥረት ብቻ ይፈታል ብሎ መገመት የትምህርትን ጥራት ማምጣት ቀርቶ አሁን ባለበት ደረጃ ለመቆየቱም ያጠራጥራል።

ለትምህርት ጥራት መምጣት ከላይ ከዘረዘሩት አካላት በተጨማሪ የወላጆችን፣ የተለያዩ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን፣ የፖለቲከኞችን፣ የምሁራንን፣ የሁሉም ቤተ እምነት የሃይማኖት መሪዎችን...ወዘተ ርብርብ የሚፈልግ ነው። በመወያየት ችግሩ ካልፈታ በስተቀር የትምህርትና የሙያ ጥራትን ማምጣት የማይታሰብ ነው።

ይህን የምለው ሚርተኛ ወይም ጨለምተኛ ሆኜ ሳይሆን ሁሉም የሙያ ዘርፎች የሚመዘዙት በትምህርት ስለሆነ ነው። የትምህርት ጥራት ሳይጠበቅ ብቃት ያላቸው መምህራንን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ ሐኪሞችን፣ ዳኞችን፣ መሐንዲሶች እና የመሳሰሉትን ባለሙያዎች ማግኘት የሚከብድ ነው። የአንድ ሀገር የትምህርት ጥራት ከተበላሸ የሁሉም የሙያ ዘርፎች እንደሚበላሽ ግለፅ ስለሆነ ጭምር ነው።

ለምን ሲባል ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቂ የትምህርት ግብዓቶች ሳይሟሉላቸውና ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠርላቸው እየተማሩ የመጡ ተማሪዎችን 12ኛ ክፍል ደርሰው ሲፈተኑ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት አላመጡም ብሎ መቆጨትም ትርጉም አልባ ቁጭት ይሆናል። ከዚህ ይልቅ ፤ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ተማሪዎችን በጥራት በማስተማር ለፈተና ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ከዚህ ውጪ የፈተና ውጤት ማሻሻልም ሆነ የትምህርትን ጥራት ለማምጣት መሞከር ያልዘሩትን ለማጨድ የመቋመጥ ያህል ነው።

በሀገሪቱ ከትምህርት ጋር በተያያዘ ያለው እውነታ ፤ ካለው የውጤት መዛነፍ ባለፈ ከትላልቅ ከተሞች ርቀው የሚኖሩ ትምህርት ቤቶች ይቅርና በትልልቅ ከተሞች ያሉ ትምህርት ቤቶች የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብዓቶች ተሟልተውላቸዋል ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

አሁን አሁንማ የማጣቀሻ መጽሐፎች፣ የሙከራ ቤቶች እና የመሳሰሉት ለትምህርት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የትምህርት ግብዓቶች ይቅርና የተማሪዎችን መማሪያ መጽሐፍት ማግኘትም ቅንጦት እየሆነ መምጣቱን ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው።በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከራከር አካል ካለ አንድ ሁለት ብሎ ካስረዳኝ ዘመኑ በመወያየት ችግሮች የሚፈቱበት ወቅት ነውና ብንወያይበት ደስ ይለኛል።

ባለፈው ዓመት አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ተግባራዊ ቢሆንም፤ተማሪዎች ግን ያለ መማሪያ መጽሐፍት ስለሚማሩ የቤት ሥራ ለመስጠት ይቸገሩ ነበር። ይህንን በተደጋጋሚ የትምህርት ኃላፊዎች በመገናኛ ብዙኃን ሲገልፁት የነበረ ጉዳይ ነው። በዚህ ዓመት በቂ የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍት ታትመው ለተማሪዎች ባይዳረሱ እንኳን ዕድሉ ያላቸው ጥቂት ተማሪዎች በሶፍት ኮፒ እንዲያነቡ በመደረጉ በጥቂቱም ቢሆን ችግሩን ፈትቷል ብዬ አስባለሁ።

> **ባለፈው ዓመት አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ተግባራዊ ቢሆንም፤ተማሪዎች ግን ያለ መማሪያ መጽሐፍት ስለሚማሩ የቤት ሥራ ለመስጠት ይቸገሩ ነበር**

ይህም ሆኖ ግን አሁንም ተማሪዎች በሶፍት ኮፒ የማግኘት ዕድሉ የላቸውም። በተለይ 85 በመቶ የሚሆነው አርሶ አደርና አርብቶ አደር በሚኖሩባቸው ራቅ ባሉ ገጠር አካባቢዎች ለሚማሩ ተማሪዎች ደግሞ የመማሪያ መጽሐፍቱን በሶፍት ኮፒ ማግኘት ቅንጦት ይሆናል።

ድሮ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባልነበረበት ወቅት የእምነት ትምህርት ቤቶች ፊደል አስቆጥረውና የየእምነቶቻቸውን መጽሐፎች ማንበብ ከቻሉ በኋላ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ስለሚገቡ ተማሪዎች የሚያስመዘግቡት ውጤትም የተሻለ እንደነበር የሚረሳ አይደለም። አሁን አሁን በእምነት ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው ትምህርት በመቅረቱም ለትምህርት ጥራት መጓደል የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል ብዬ አስባለሁ። በሀገር በቀል እውቀት አለመጠቀም ችግር ነው የሚባለውም ከዚህ የተነሳ ይመስለኛል።

ይህ ማለት ከእምነት ትምህርት ቤቶች ተምረው የሚመጡ ተማሪዎች በደንብ ማንበብና መጻፍ ችለው፤ ቁጥር ቆጥረውና አራቱን የሂሳብ መደቦች ማስላት ችለው ስለሚመጡ በመደበኛው ትምህርት ቤቶች ብዙ ጊዜ የሚጀምሩት ከ3ኛ ክፍል፣ አልፎ አልፎም ከ2ኛ ክፍል ነበር። በደርግ ጊዜ ሲሰጥ የነበረው መሠረተ ትምህርትም ተማሪዎች ማንበብና አራቱን የሂሳብ መደቦች እንዲያውቁ አስተዋጽኦ ነበረው።

ይህንን ተሞክሮ መነሻ በማድረግ ይመስለኛ የመጀመሪያ ደረጃ የአንደኛ ሳይክል ተማሪዎች (በተለይ ከ1ኛ ክፍል እስከ 3ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች) ማንበብና መጻፍ፣ አካባቢያቸውን መገንዘብና አራቱን የሂሳብ መደቦች በትክክል ማስላት ከቻሉ ሌላ ውስብስብ ነገር ማወቅ ስለማይጠበቅባቸው በየጊዜው በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴና የክፍል ውስጥ ተከታታይ ምዘና እየተሰጣቸው ወደሚቀጥለው ክፍል ማለፍ ይችላሉ ተብሎ የነበረው።

ነገር ግን በታችኛው እርከን ባሉ የትምህርት ባለሙያዎችና በመምህራን የተሳሳተ ግንዛቤ ከ1ኛ ክፍል እስከ 3ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች መድገም የለባቸውም እየተባለ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ፣ ቁጥር በአግባቡ የማይቆጥሩና አራቱን የሂሳብ መደቦች የማያሰሉ ተማሪዎች ወደሚቀጥለው ክፍል እንዲዛወሩ መደረጉም ሌላው ለትምህርት ጥራት መጓደል አንዱ መንስኤ ይመስለኛል። ችግሮችን ከታች ወረድ ብለን ማየት ይኖርብናል የምለው እነዚህንና መሰል ጎዳዮችን ለማየት የተሻለ እድል ስለሚፈጥር ነው።

# የገዳ ሥርዓት

## የኢትዮጵያ እና ኬንያን ወዳጅነት የማጠናከር አቅሙ የጎላ መሆኑ ተገለጸ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዶላ፡- የገዳ ሥርዓት የኢትዮጵያ እና ኬንያን ወዳጅነት የማጠናከር አቅሙ የጎላ መሆኑን ኢፕድ ያነጋገራቸው ኬንያውያን ገለፁ፡፡

በጉጂ አባገዳዎች ዘንድ የሚፈፀመው 75ኛው የ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መርሐ ግብር ተካሂዷል፡፡

በኬንያ የታና ሪቨር ማኅበረሰብ ምክር ቤት ተወካይ ሚስተር ኢስማኤል ኮዶቦ እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ እና የኬንያ ወዳጅት ዘመናትን የተሻገረ ነው፡፡ መሰል ሁነቶች ደግሞ የበለጠ ትስስር የመፍጠር አቅማቸው የላቀ ነው፡፡

የጉጂ አባገዳዎች የ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መሠረታዊ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብን በሚገባ የተረዳ እና ለትውልድ ትልቅ ማስተማሪያ እንደሆነ የገለጹት ኬንያውዩ፤ በኬንያ ያሉ ኦሮሞዎች በዚህ ደረጃ የገዳ ሥርዓትን የማያከብሩ መሆኑን ጠቁመው፣ በተለይም ነባሩን እሴት እና የቆየ የአባቶችን ባህል ማቆየት ባለመቻሉ የአባ ገዳዎች የሥልጣን ርክክብ አለመኖሩን ጠቅሰዋል፡፡

ይሁንና ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የገዳ ሥርዓት ጥንታዊ ትውፊቱን ይዞ በመቆየቱ ታሪክን ለትውልድ ማስተላለፍ መቻሉን አንስተዋል፡፡

ይህ በኬንያ ለሚኖሩ ኦሮሞዎች ኩራት ነው ብለው፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን ወዳጅነትም ለማጠናከር ሚናው የጎላ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ሁለቱ ሀገራት በምጣኔ ሀብት ትስስራቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ መሆናቸውን የተናገሩት ሚስተር ኢስማኤል ኮዶቦ፤ በባህል ዘንድም ያለው ቅርርቦሽና ተመሳሳይነት የሁለቱን ሀገራት የቆየ ወዳጅነት ወደ ተሻለ ምዕራፍ የማሸጋገር አቅም አለው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ሌላኛው የመርሐ ግብሩ ተሳታፊ ሚስተር አህመድ መሐመድ ቀደም ሲል  የገዳ ሥርዓት መገለጫ የሆነውን እሬቻ በዓል በማስመልከት ቢሾፍቱ መገኘታቸውን ተናግረዋል፡፡

አሁን ደግሞ ስምንት ዓመታትን ጠብቆ ለሚካሄደው የጉጂ አባገዳዎች የ‹‹ባሊ›› ርክክብ ላይ መገኘቴ መስማትን እና ማየትን ብቻ ሳይሆን ሆኖ የመኖርን ያክል ስሜት ሰጥቶኛል›› ብለዋል፡፡

በገዳ ሥርዓት መሠረት በጉጂ አባገዳዎች መካከል ያለው የሥልጣን ርክክብ ዓለም ላይ ያለው የዴሞክራሲ አስተምህሮን የቀደመ ሲሆን፤ በዚህም ኢትዮጵያ እና ኬንያ ቀዳሚዎች እንደነበሩ ማወቅ ያስችላል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ይሁንና ይህ ባህል ዘመናዊነት እየተጫነውና በሚገባ ባለመጠበቁ በኬንያ መሠረቱን ማጣቱን ጠቅሰው፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ግን በዚህ ደረጃ ዕሴቱ ተጠብቆ መኖሩ ለኬንያውያን ትልቅ ዕድል መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የሁለቱን ሀገራት ወዳጅነትም በበለጠ ለማጠናከር አንዱና ትልቁ ታሪካዊ መሠረት ሆኖ ማገልገል ይችላል ነው ያሉት፡፡

ሌላኛው የ ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መርሐ ግብሩ ተሳታፊ ሚስተር ዲማ ዑመር እንደተናገሩት፤ የገዳ ሥርዓት ጥሩ መሠረት ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ እና ኬንያን ወዳጅነት አሁን ካለው በበለጠ ለማስተሳሰር ዓይነተኛ መንገድ የመሆን አቅም አለው፡፡

በሁለቱም ሀገራት መካከል ተመሳሳይ ሥነ ልቦና፣ ቋንቋ፣ ልማድ እና ባህል ትስስር ያላቸው ሕዝቦች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በመሆኑም በዚህ ሥርዓት ላይ የሚያጠነጥን ጥናትና ምርምሮችን ማድረግና የሁለቱን ሕዝቦች የቆየ ትስስር በጉልህ ደረጃ ማሳደግ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የገዳ ሥርዓት በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የባህልና ትምህርት ድርጅት (ዩኔስኮ) ውስጥ ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አንዱ ተብሎ መመዝገቡ የሚታወስ ነው፡፡

# የእንስሳት ሀብት ልማቱ ተስፋና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አይደለም።

በዘርፉ በተፈለገው ፍጥነት ልማት ማምጣት እንዳይቻል ያደረገ የፖሊሲ ክፍተት አለ ያሉት ዶክተር ደሳለኝ፤ የእንስሳት ልማቱ አልፎ አልፎ የአቅርቦት እጥረት በሚያጋጥምበት ጊዜ ወይም ከፍተኛ ምርት ለውጭ ገበያ በሚያስፈልግበት ወቅት በዘመቻ መልኩ ስትራቴጂዎች የሚቀረጹለት ነው ብለዋል።

የዶክተር ደሳለኝ ጥናት ግኝት እንደሚያሳየው የእንስሳት ልማት ዘርፉ በዘልማድ ከሚከናወነው የተሻለ ደረጃ ላይ አልደረሰም። በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚደረጉ ሙከራዎችና ጥረቶች እንዳሉ ሆነው ዘርፉ በፖሊሲ ባለመደገፉ ውጤት ሊመጣ አልቻለም። ጥሩ ፖሊሲ ቢኖር እንኳን ትግበራውን ለማከናወን የሚያስችል መዋቅር አልተዘረጋም።

የእንስሳት ምርቱ ከሀገሪቱ ሕዝብ ብዛት እኩል እያደገ ባለመሆኑ ለወደፊቱ ከእንስሳት የሚገኙ አልሚ የሚባሉት ምግቦች እየጠፉ ይሄዳሉ። በዚህም ኢትዮጵያ ብዙ ችግር ውስጥ ልትገባ ትችላለች ሲሉ የጠቆሙት ዶክተሩ፤ በተጨማሪም ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬም እየቀነሰ ሲሄድ የሀገር ኢኮኖሚን ይጎዳል ሲሉ አመላክተዋል።

በፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ጥናት ማዕከል ተመራማሪው ታደሰ ኩማ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የእንስሳት ዘርፉ ለሀገራዊ ልማት ተኪ የሌለውና በምግብ ዋስትና፣ በውጭ ምንዛሬና በሥራ ዕድል ፈጠራ ትልቅ ቦታ  የሚይዝ ነው።

ባለንበት ወቅት የእንስሳት ዘርፍ በርከት ያሉ ፈተናዎች እየገጠሙት ይገኛል ያሉት ዶክተር ታደሰ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው የመኖ እና ውሃ ሀብት እጥረትና ከአየር ንብረት መዛባት ጋር ተያይዞ የእንስሳት ዕድገትና ምርታማነት ውስን ሆኗል ይላሉ።

ተመራማሪው እንደሚናገሩት፤ ለዘርፉ ወደኋላ መቅረት የመጀመሪያውና ትልቁ ማነቆ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚመራ እውቀትን ማዕከል ያደረገ አለመሆኑ ነው። አብዛኛው የእንስሳት ዘርፍ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ በሚመሩ አነስተኛ አርሶ አደሮች እጅ የሚመራ ነው። በፖሊሲና ስትራቴጂ ደረጃ ያለው የመንግሥት ድጋፍም ቢሆን ወደ ሰብል ልማት ያዘነበለ ነው። የእንስሳት ዘርፉን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች ቢኖሩም መሬት የመርገጥ ውስንነት አለባቸው።

ሌላኛው የእንስሳት ዘርፉ ፈተና ከተቋም ጋር የሚያያዝ መሆኑን አመላክተው፤ አንድ ሀገር የሚለማው ጠንካራ ተቋም ሲኖር መሆኑን በመጥቀስ፣ የእንስሳት ዘርፉ አንድ ጊዜ ሲደራጅ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲፈርስ እንደ ተቋም ተረጋግቶ የመሥራት ዕድል እንዳላገኘ ይገልጻሉ።

ዘርፉ እንዲያድግ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች በጠቆሙበት ንግግራቸው፤ የእንስሳት ልማትን መንግሥትና አነስተኛ አርብቶ አደሮች ብቻ ሊደግፉ አይችሉም፤ የግል ባለሀብቶች በብዛት መሳተፍ አለባቸው። ከፍተኛ ሀብት እንዲሁም በዘርፉ ከፍ ያለ እውቀትና ልምድ ያላቸው ብዙ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ባለሀብቶች መኖር አለባቸው። ጅምሩ ቢኖርም አንዳንዶቹ ከገቡበትም ሲወጡ ይታያል ብለዋል።

በተለይም ከአካባቢ መራቆት የተነሳ አቅርቦቱ ቀንሶ ፍላጎቱ በጨመረው የእንስሳት መኖ ላይ ባለሀብቶች ለዘለቄታው የሚሰማሩበትን መንገድ መቀየስ ያስፈልጋልም ብለዋል።

የኢትዮጵያ እንስሳት ምርታማነት ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር ከ25 በመቶ እንኳን የዘለለ አይደለም። አንድ አላስፈላጊ አካላቱ የወጡለት የበሬ ስጋ ብንመዝን 110 ኪሎ አካባቢ ነው። በሌሎች ሀገራት 400 እና 500 ኪሎ ይመዝናል የሚሉት ታደሰ ኩማ (ዶ/ር)፤ የእንስሳትን ምርታማነት በተለያየ ደረጃ መቀየር እንደሚያስፈልግና፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የተከተለ አመራርት ዘዴን ይፈልጋል ብለዋል።

አብዛኞቹ የቀንድ ከብቶች የሀገር ውስጥ ናቸው፤ ከውጭ ያመጣናቸው ይበልጥ ምርታማ የሆኑ ዝርያዎች ሁለት በመቶ ብቻ ናቸው። ከውጭ መጥቶ የተዳቀለ ዝርያው ከፍ ያለው ዶሮ ብቻ ነው፤ የተቀሩት ሁሉ ትንንሽ ናቸው። የራሳችንን ዝርያዎች ይዘን ከዓለም የተሻለ ምርት ከሚሰጡ ዝርያዎች ጋር በማዳቀል ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አለብን ሲሉ መክረዋል።

በሁለቱ ተመራማሪዎች በቀረበው ሃሳብ ላይ አስተያየታቸውን የጠየቅናቸው በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፍቅሩ ረጋሳ (ዶ/ር) ፤ በግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ውስጥ የእንስሳት ዘርፉን ለማሳደግ የሚረዱ ሰፋ ያሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎች አሉ ብለዋል።

በመዋቅር ደረጃም ከዚህ በፊት በብዙ መልኩ ትኩረት ያልተሰጠው የአርብቶ አደር አካባቢ በተቋም ደረጃ እውቅና አግኝቶ የመስኖና ቆላማ አካባቢዎች ሚኒስቴር እንዲቋቋም ተደርጓል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተቀመጡ ስትራቴጂዎችን ወደተግባር ቀይሮ እየሠራ በመሆኑ ከዘርፉ መጠቀም ከሚገባን አንጻር ይጎድሉ የነበሩ ነገሮችን ለመድረስ ጥረት እየተደረገ ነው ያለው ይላሉ።

ከዚህ ቀደም የግብርና ሚኒስትር የሆነ ሰው እንኳን ግብርና ሲባል የተወሰነውን ክፍል ይዞ የሚሮጥ እንደነበር ያወሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ አሁን በሚገርም ሁኔታ በጠቅላይ ሚኒስትር ደረጃ የሌማት ቱርፋት ኢኒሼቲቭ ከተጀመረ አንድ አመት አልፎታል። እንደየ ክልሉ አውድ በክልል መንግሥታት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የእንስሳት እርባታ ቦታዎች በመገኘት እንስሳት የሚያረቡትን ባለሙያዎች በማበረታታትና ለዘርፉ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ በማቅረብ ዘርፉን እየደገፉ ይገኛሉ። በዚህም ከነበረው ሁኔታ አንጻር በምርትና ምርታማነትና በግብዓት አቅርቦት ትላልቅ መሻሻሎች እያየን ነው ብለዋል።

አክለውም፤ አዲስ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ቀረጻ ተጠናቆ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ የሚጸድቅበት ደረጃ ላይ ይገኛል ሲሉም የእንስሳት ዘርፉን ችግሮች ለመፍታት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ተመራማሪዎቹ ያሉትን ክፍተቶች ዳስሰው ወደፊት መስተካከል የሚገባቸውን ነገሮች እንደ ግብአት እንድንወስድ ያቀረቡት ምክረ ሃሳብ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረንና ወደፊትም ምን ዓይነት ክፍተቶችን ማስተካከል እንዳለብን  ግንዛቤ የጨበጥንበት ነውም ብለዋል።

# አፍሪካ የተሻለ የጤና አገልግሎት አማራጭ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአፍሪካ ሲዲሲ እቅዶች አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፤ የአፍሪካ ሲዲሲ የአባል ሀገራትን የሕዝብ ጤና አገልግሎት ለመደገፍ እየሠራ ነው።

የአፍሪካን የጤና አጀንዳዎች ወደ ፊት ለማራመድ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ገልጸው፤ ሲዲሲ አፍሪካ አስፈላጊውን የቴክኒክ ድጋፍ እና የማማከር ተግባሩን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

በአህጉሩ ዓለም አቀፋዊ ደረጃውን የጠበቀ ምርምር የሚካሄድበት እና ግኝቶች የሚወጡበት የላቦራቶሪ ሥርዓት በመገንባት ረገድም ሊሠራ እንደሚገባም ጨምረው ገልጸዋል።

ጤናን የተመለከቱ ተቋማዊ ጉዳዮች በሥርዓት እንዲመሩ እና አፍሪካ የተሻለ የጤና አገልግሎት አማራጮች እንዲኖራት ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ተናግረዋል።

የበሽታ አደጋዎችን በፍጥነት እና በብቃት የመለየት፣ የመከላከል፣ የመቆጣጠር እና ምላሽ የመስጠት አቅምን ማጠናከር እንደሚገባ ገልጸው፤ በዚህም  «አጋርነት ለአፍሪካ ክትባት» የሚል ፕሮግራም ተቀርጾ 60 በመቶ የሚሆነውን የአፍሪካ ክትባት በአህጉሩ ውስጥ ለማምረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

በአህጉሩ ሊከሰቱ ለሚችሉ ወረርሽኞች እና ሌሎች በሽታዎች መረጃን መሠረት በማድረግ የመከላከል እና ሲከሰቱም ፈጣን ምላሽ እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ተደራሽነቱን ለማሻሻል በጨረታ እና በግዢ ምክንያት የሚባክነውን ጊዜ እና ገንዘብ ለመቆጠብ መድኃኒቶች እና ክትባቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ እየሠራ መሆኑን እና በዚህም የአህጉሪቱን የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ማስፋፋት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

ወባ፣ ኮሌራ፣ ኢቦላ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስ እና ሌሎች ተላላፊ እና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ ልዩ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ኮሌራ እና መሰል በሽታዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየተስፋፉ በመሆኑ ችግሩን ለመቋቋምም ስትራቴጂክ ዕቅድ አውጥተው እየሠሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በተጨማሪም የኤች አይ ቪ ቫይረስ አሳሳቢነት ላይ ከ30 በላይ የሀገራት ጤና ሚኒስትሮች ጋር ውይይት በማድረግ ሀገራቱ ልምዶቻቸውን አካፍለዋል ብለዋል፡፡

ማዕከሉ አሁን ባለው አቅም ዓላማውን ማሳካት እንደሚከብደው ገልጸው፤  ኅብረቱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው በ37ኛው የመሪዎች ጉባኤ ላይ ጥያቄ ማቅረባቸውን አስታውሰዋል፡፡

# «ኢትዮጵያ በበጋ ስንዴና በአረንጓዴ ዐሻራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዐሻራም የደን ሽፋንን ከማሳደግ በተጨማሪ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ መቻሉን ገልፀዋል።

በተለይ ኢትዮጵያ ስንዴን ከውጭ ከማስገባት ወጥታ ለውጭ ገበያ እያቀረበች ያለችበትን ልምድ ለአፍሪካም ማካፈል ትሻለች ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ። አፍሪካም ከኢትዮጵያ ትምህርት በመውሰድ አየር ንብረት ለውጥ እያሳደራቸው ያሉትን ተጽዕኖዎች መቋቋም አለባት ብለዋል።

ሀገሪቱ የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ግብርናን በማዘመን የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ከግብርና ልማቱ ጋር በማስተሳሰር እየሠራች ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የተመጣጠነ የምግብ ሥርዓትን ለመተግበርም በሌማት ትሩፋት ላይ ትኩረት መደረጉን አንስተው፤ ሀገራት የኢትዮጵያን ልምድ በመውሰድ አህጉራዊ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በጋራ መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

የአፍሪካ 90 በመቶ ግብርና ዝናብ ላይ ጥገኛ መሆኑን ገልፀው፤ ግብርናውን  ለማዘመንና በውሃ ላይ የተመሠረተ የግብርና ልማት ለማካሄድ አሁንም ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን  ተናግረዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ የአህጉሪቱን ግብርና እየፈተነ መሆኑን አውስተው፣ የመሠረተ ልማቶች አለመሟላት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነትና ሌሎች ችግሮች የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ተግዳሮት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የአፍሪካን ግብርናን ለማዘመንና ለማሳደግ በምርምር የተደገፈ ድጋፍና ክትትል እንደሚያስፈልግና የፖለቲካ ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ በጉባኤው ላይ ተገልጿል።

የአህጉሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የትብብር ጊዜው አሁን እንደሆነ መሪዎችና ሙያተኞች መገንዘብ እንዳለባቸው ተናግረዋል። ለዚህም ዘላቂ የግብርና ስትራቴጂን፣ የጋራ ራዕይ፣ እውቀት፣ የተባበረ ጥረትና ሀብትን አቀናጅቶ መሥራት እንደሚያፈልግ ተናግረዋል።

ከ37ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ጎን ለጎን አፍሪካ በምግብ  ራሷን በምትችልበት ሁኔታ፤ የአየር ንብረት ለውጥ መፍትሔዎች እና ለምግብ ሥርዓት ለውጥ የጋራ እርምጃ ሊተገበሩ በሚገቡ እቅዶች ላይ ያተኮረ ውይይት በዓድዋ ድል መታሰቢያ የፓን-አፍሪካ አዳራሽ ትናንት ሲካሄድ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እና የቻድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሰክሰስ ማርሳን ጨምሮ  ሚኒስትሮችንና ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮችና ከፍተኛ የዘርፉ ባለሙያዎች  ተገኝተዋል።

# ከኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ በተጓዳኝ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሀገራት መሪዎች ጋር የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸውን ገልጸዋል። ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋርም ስኬታማ ውይይቶች ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ፤ ከሞሮኮ እና አልጄሪያ አቻቸው ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነት በሚጠናከርባቸው ጉዳዮች ላይ መምከራቸውንም ቃል አቀባዩ ገልጸዋል።

በጉባኤው ተሳታፊ ከሆኑ የተለያዩ ሀገራት ጋር ወዳጅነቱ እንዲጠናከር እና ያሉን ጥቅሞች በተጨባጭ ውጤት የሚያመጡ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑንም አክለዋል።

ከሀገራት ጋር የተደረጉ የሁለትዮሽ ውይይቶችና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የተደረጉ ምክክሮች ውጤታማ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ መሐሙድ የመሩት ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ለሁሉም ሀገራት በተደረገው ልክ ደማቅ አቀባበል እንደተደረገላቸው ገልጸዋል።

የተለመደው አሠራር መሪዎች ሲመጡ አቀባበል ብቻ ሳይሆን ጥበቃ የሚደረገውም በአስተናጋጅ ሀገር መሆኑን አንስተው በፕሬዚዳንቱ በኩል ግን የጥበቃ ድጋፉን አልቀበልም ማለታቸውን ቃል አቀባዩ አስረድተዋል።

እንዲሁም ወደ ስብሰባ እንዳልገባ ተከለከሉ በሚል የቀረበው አስተያየትም የተሳሳተ እና ተገቢ አለመሆኑን ገልጸዋል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ለሀገር ምጣኔያዊ ዕድገት ተስፋ የተጣለበት የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ

**ማህሌት አብዱል**



ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት የምትመራበትን የግብርናውን ክፍለ ኢኮኖሚ ዘርፍ ለማሳደግና ምጣኔ ሀብቷን በዚያው ልክ ከፍ ለማድረግ የሚያስችሏትን በርካታ የልማት መርሃግብሮች ነድፋ በመተግበር ላይ ትገኛለች:: በተለይም በየዓመቱ በእቅድ ተይዘው የሚሠሩት የግብርናው ዘርፍ የልማት መርሃግብሮች ተጨባጭ ውጤት እንዲያመጡ ብርቱ ጥረትና ክትትል ስታደርግ ቆይታለች:: በስንዴ ልማት መስክ የተመዘገበው ውጤትም የዚሁ ጥረት ማሳያ ተደርጎ የሚጠቀስ ነው::

ዘርፉን የሚመራው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከሌሎች ባለድርሻ ተቋማትና አካላት ጋር በመቀናጀት እያከናወነ ያለው የልማት ሥራም ይበል የሚያሰኘው ሆኗል:: በአንፃሩ ደግሞ ለዓመታት ሲንከባለሉ በመጡ ችግሮች ሳቢያ ዛሬም አርሶአደሩ ከምርቱ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ይደመጣል:: ይህንን ችግር በመፍታት ረገድም ሚኒስቴሩ ደፋ ቀና እያለ ስለመሆኑ ከሰሞኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ቋሚ ኮሚቴ ሲናገር አድምጠናል::

ቋሚ ኮሚቴው የሚኒስቴሩንና የግብርና እና የተጠሪ ተቋማቱን የስድስት ወራት አፈፃፀም በገመገመበት ወቅት የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ባቀረቡት ሪፖርት፤ የአርሶ አደሩን ኑሮ ለማሻሻልም ሆነ ሀገሪቱ ከዘርፍ የላቀ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማድረግ ባለፉት ስድስት ወራት በርካታ ሥራዎች ተከናውኗል:: ከእነዚህም መካከል የማዳበሪያና የዘር አቅርቦት በበቂ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የተደረገው ርብርብ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው::

‹‹ዘንድሮ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ጅቡቲ የደረሰው ባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ ነው፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጅቡቲ ከደረሰው ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ውስጥ ሰባት ሚሊዮን ኩንታሉን ሀገር ውስጥ ማስገባት ችለናል›› በማለት በዚህ ዓመት ከሚያስፈልገው ማዳበሪያ 36 ነጥብ ስምንት በመቶ ሀገር ውስጥ መግባቱን ያመለክታሉ::

ባለፈው ምርት ዘመን በተለይም መኸር ላይ የተስተዋለውን የአፈር ማዳበሪያ የአቅርቦት ችግር ለመፍታት በተደረገው ሪፎርም ማዳበሪያ በወቅቱና በተሻለ ገንዘብ መግዛት መቻሉን ያብራራሉ:: በአፈር ማዳበሪያ ግዥ የመንግሥትን የድጎማ ጫና በመቀነስ በማዳበሪያ ግዢ ውስጥ 20 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን ሲያስረዱ፤

ለማዳበሪያ ግዢ በተመደበው 71 ቢሊዮን ብር 1 ነጥብ4 ሚሊዮን ቶን (19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል) ማዳበሪያ መገዛቱንም ያመለክታሉ:: ‹‹2016/17 ፍላጎት ሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ቶን ወይንም 23 ሚሊዮን ኩንታል ግዢ ለመፈጸም እቅድ ዘንድሮ ለማዳበሪያ ግዢ የተመደው አምና ከተገዛው ጋር የስድስት ሚሊዮን ኩንታል ብልጫ አለው›› ሲሉም ይጠቅሳሉ::

ሚኒስትሩ ሪፖርታቸውን ለእንደራሴዎቹ ሲያብራሩ፤ አምና የተመደበው አንድ ቢሊዮን እንዲሁም የትግራይን ጨምሮ 59 ቢሊዮን ዶላር 12 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዢ ተፈፅሟል:: አምና 12 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ለመግዛት መንግሥት ድጎማ አድርጎ የነበረው 21 ቢሊዮን ብር ነበር:: ዘንድሮ 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ተገዝቶ ድጎማ የተደረገው 16 ቢሊዮን ብር ብቻ ነው:: የበልግና የመስኖን እርሻ ሊሸፍን የሚችል ማዳበሪያ ሀገር ውስጥ ገብቷል:: በቀን 150 ሺ ኩንታል ማዳበሪያ እየተጫነ ይገኛል:: በተያዘው ፍጥነት ከቀጠለ ዘንድሮ የማጓጓዝ ሥራው ግንቦት ወር ላይ ይጠናቀቃል::

ዘንድሮ የአርሶአደሩ የማዳበሪያ ፍላጎት ጭማሬ ማሳየቱን አመልክተውም፤ ‹‹ከዚህ በፊት አርሶ አደሩ በዚህ ልክ የማዳበሪያ ጥያቄ አልነበረውም፤ አሁን እየጠየቀ በመሆኑ ጥያቄውን ለመመለስ ማቅረብ አለብን›› ሲሉ ተናግረዋል:: ማዳበሪያ አቅርቦት ላይ ጨርሰናል ተብሎ ለአንድ አፍታም መዘናጋት እንደማይኖር አስገንዝበዋል:: አርሶ አደር ጋር ደርሶ ምርት ላይ እስኪውል ድረስ ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን መደረግ እንዳለበትም ጠቅሰው፤ ለዚህ ትግበራ ሚኒስቴሩ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ መሆኑም አስረድተዋል::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አማራ ክልልና ተመሳሳይ ትኩረት የሚሹ አካባቢዎችም መኖራቸውን ጠቁመው ‹‹በጸጥታ ችግር ምክንያት ማቅረብ በሚገባን ያክል ግብዓት ለማቅረብ አልቻልንም›› ይላሉ:: ይሁንና ሚኒስቴሩ በአሁኑ ወቅት ከሚመለከታቸው ጋር ንግግር ማድረጉን ነው ያመለከቱት::

ኢትዮጵያ በምግብ ሉዓላዊነቷን ለማስከበርና ለማረጋገጥ በምታደርገው ጥረት ውስጥ እንደ ከዚህ ቀደሙ የመኸር ወቅትን ብቻ ጠብቆ አንድ ጊዜ ማምረት አዋጭ አለመሆኑን ለምክር ቤቱ ያስረዳሉ:: በመሆኑም ግብርናው ሁሉንም ወቅቶች ባማከለ መልኩ ወደ ማምረት መሸጋገሩን ያመለክታሉ:: ‹‹መኸርን ስንጨርስ ወደ መስኖ አቅደን መግባት፣ መስኖን ስናጠናቅቅ በልግን ወደ ሥራ በማስገባት ምርታማነትን ማሳደግ ላይ አተኩረናል›› ሲሉም ይገልፃሉ::

እንደሀገር በበጋ መስኖ ልማት እየተከናወነ ስላለው የስንዴ ልማት ዙሪያም እንደተናገሩት፤ የስንዴ ምርት ከአምስት ዓመት በፊት ትግበራ ሲጀመር በመኸር የሚመረተው 1 ነጥብ 75 ሚሊዮን ሄክታር ነበር:: አሁን በመኸር የሚመረተው 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ደርሷል:: በየወቅቶቹ የምርት ግኝቱ ወሳኝና ተቀራራቢ ምርት ላይ እየደረሰ መጥቷል:: በዚህ ምክንያትም በሁለቱ ወቅቶች የሚመረተው ስንዴ ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ቀዳሚ የስንዴ አምራች ያደርጋታል::

‹‹መጠኑ ቢያንስም በበልግ ወቅትም ስንዴ ይመረታል:: ባለፈው ዓመት ከ 300 ሺ ሄክታር በላይ በበልግ ስንዴ ተመርቷል›› ያሉት ዶክተር ግርማ በሌላ በኩል ደግሞ በየክልሉ የተለያዩ ጸጋዎች እና አቅሞች በመጠቀም አበረታች ሥራ እየተሠራ ስለመሆኑ ያስረዳሉ:: ይሁንና ሁሉም አካባቢዎች በስንዴ ምርት አንደኛ መውጣት እንደማይችሉ ጠቅሰው፤ አንዳንድ አካባቢ መስራት የሚችለው በቆሎ በማምረት ሊሆን እንደሚችል፤ ሌላው ጋር ደግሞ ወሳኝ አቅም ያለው በእንስሳት ርባታ ሊሆን እንደሚችል ከግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚገባ ይናገራሉ::

በመሆኑም አካባቢዎቹ እንደየጸጋቸውና አቅማቸው እንዲያመርቱ መደረግ እንዳለበት ይገልፃሉ:: በዚህ ረገድ ግብርና ሚኒስቴር በሁሉም አካባቢ ያለውን ጸጋና አቅም ለመጠቀም የሚያስችል ትግበራ እንዲገባ ማድረጉን ያመለክታሉ:: በተለይም ከግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩትና ከግብርና ምርምር ጋር በመሆን በተለይ ለታዳጊ ክልሎች የግብርና ሽግግር ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱን ነው የጠቀሱት::

‹‹ጋምቤላ ምን ላይ ማተኮር እንዳለበት፣ አፋር ክልል ምን ላይ ማተኮር እንዳለበት፣ ሶማሌ ክልል ምን ላይ ማተኮር እንዳለበት፣ ደቡብ፣ ምዕራብ ምን ላይ ማተኮር እንዳለባቸው ለይተናል›› ይላሉ:: የአራት ክልሎች የግብርና ፍኖተ ካርታ መጠናቀቅን፤ በአሁኑ ወቅት እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር እየተገባ መሆኑን ያስረዳሉ:: ክልሎችን የመደገፍና በእቅዱ መሠረት ወደ ሥራ መግባታቸውን የማረጋገጥ ሥራ የሚሠራ መሆኑንም ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢትዮጵያ የሥርዓተ ምግብ ሽግግር ማድረግ እንድትችል ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው ሲሉም ሚኒስትሩ ጠቁመዋል:: ‹‹ከዚህ በፊት ስናወራ የነበረው ስለምርትና ምርታማነት ብቻ ነበር:: አሁን አስተሳሰቡን ቀይረናል:: ከምርት እስከ ማዕድ ድረስ ያለው ሙሉ የሂደት ስንሰለቱ መታየት አለበት›› ይላሉ:: አርባ ምንጭ የተመረተው ሙዝ ተገቢ የማጓጓዣ አቅርቦት ተመቻችቶለት ገበያ መቅረብ ካልቻለ በአካባቢው መመረቱ ብቻ በቂ አለመሆኑን ለአብነት ጠቅሰው ያስረዳሉ:: በመሆኑም አሁን በቀጠለው የሥርዓተ ምግብ ሽግግር ምርት ላይ የሚሠራው ምርታማነትን መጨመር ላይ እንዲያተኩር፣ የማጓጓዣ ሥርዓቱ ላይም መሠራት እንዳለበት መግባባት መኖሩን አስገንዝበዋል::

በተጨማሪም እንደቲማቲም ያሉት ምርቶች በሎጅስቲክስ አቅርቦት ወደ ገበያ ባለመውጣታቸው ምርቱ እየበሰበሰ የሚጣልበት አጋጣሚ መኖሩን ለእንደራሴዎቹ ተናግረዋል:: የምርት ብክነቱን ለመከላከልም የምርት ማዕከላትን ከገበያ ማዕከላት ጋር በሎጅሲቲክስ የማገናኘትና የማስተሳሰር ሥራዎች ለማሳካት ሥራ መጀመሩን ነው የጠቆሙት::

ከዚህ ጋር ተያይዞ አሁን በምርቶች ላይ የሚታያውን የዋጋ ንረት አስመልክተውም ‹‹ለዋጋ ንረቱም ዋና መፍትሄ የሚሆነው ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ብቻ ነው:: በሌማት ትሩፋት፣ በስንዴ ምርትና በሌሎቹም የግብርና ዘርፎች የተጀመሩ ሥራዎች ተስፋ የሚሰጡ ናቸው:: እነዚህን በማሳደግ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል›› ሲሉ አብራርተዋል::

እንደ አቶ ግርማ ገለፃ፤ የወተትና የስጋ ምርት ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በወተት 31 ከመቶና ስጋ 74 በመቶ እድገት አሳይቷል:: የማርና የእንቁላል ምርት አፈጻጸም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በማር 57 በመቶና በእንቁላል ምርት 52 በመቶ ዕድገት ተመዝግቧል። በመሆኑም ተግባሩ የሌማት ትሩፋት ሥራ ተጨባጭ ውጤት ማሳየቱን እንሚያመለክት መገንዘብ ይቻላል::

በሌላ በኩልም በቡና ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ካምና ያነሰ ውጤት ባይመዘገብም ነገር ግን በዋጋ መቀነሱን ሚኒስትሩ አልሸሸጉም:: ለዚህም ምክንያቱን ሲያስረዱ ‹‹አንድም የምርት ጥራት ነው:: በመሆኑም በቀጣይ የምርት ጥራት ማሳደግ እና ተወዳዳሪ መሆን አለብን›› ሲሉ ነው የገለፁት::

የምግብ ደህንነት እና ጤንነት ጭምር መረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን ሲገልጹ፤ አንዳንድ ምርቶች ተጠቃሚ ጋር እስኪደርሱ ድረስ በአግባቡ ካልተያዙ ችግር ይፈጥራሉ:: በመሆኑም ይህንን የሚመራ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቷል:: ከዚህም ባሻገር መፍትሄ ሊያመጡ የሚችሉ 22 የሚደርሱ ቁልፍ የሆኑ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከተለምዶ አመራረት አውጥተው ማስፈንጠር የሚችል ትግበራ መጀመሩን አመላክተዋል:: ትግበራውን የሚያስተባብር 15 ሚኒስትሮች የተካተቱበት የሚኒስትሮች አብይ ኮሚቴ መቋቋሙንም አክዋል::

እንደአቶ ግርማ ማብራሪያ፤ የዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት ሰሞኑን ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአግሪኮላ ሽልማት ያበረከተው ኢትዮጵያ በምግብ ዋስትና እና በተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት አመራርና ቁርጠኝነት ላሳዩት አርአያነት ያለው ተግባር ነው:: ጅምሩን በመመልከት ስኬታማ እንደሚሆንና ከግብ እንደሚደርስ በማመናቸው ነው:: ይህ ግብርናው ሽግግር ላይ መሆኑን የሚያሳይ ነው:: ይሁንና ስትራቴጂካዊ በሆነ መልኩ ከጅምሩ እስከ ማዕድ ድረስ መመራት ይገባዋል::

በሌላ በኩል ባለፉት ስድስት ወራት ግብርናው ከወጪ ንግድ 1 ነጥብ 35 ቢሊዮን ዶላር ማስገባቱን ያመለክታሉ:: የወጪ ንግዶች ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 10 በመቶ ጭማሪ ሲያሳይ በገቢ 195 ሚሊዮን ዶላር ቅናሽ ማሳየቱን፤ ከእቅዱ አንጻር ጉድለቶች እንዳሳየ ተናግረው:: የማካካሻ ሥራ እንደሚተገበር ጠቁመዋል::

ሚኒስትሩ ከዘር አቅርቦት ጋር በተያያዘም እንደተናገሩት፤ ባለፉት ሶስት ዓመታት በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የነበረውን ወደ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ ታቅዷል:: ዘንድሮ ወደ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ለማሳደግ ትኩረት ተደርጓል:: በዚህ ረገድም መንግሥትና ባለድርሻ አካላት ለግብርና የሰጠው ትኩረትና ድጋፍ፣ ከክልሎች ጋር በጋራ በመወያየት ተቀራርቦና ተደጋግፎ የመሥራት መልካም ጅምሮች መኖራቸው ለዘርፉ መልካም አጋጣሚ መሆናቸውን አስገንዝበዋል::

በስድስት ወራቱ በአፈፃፀም ረገድ የተለዩ ድክመቶች እንደነበሩ ሚኒስትሩ ተናግረው፤ በዋነነትም በየደረጃው ያሉ አደረጃጀቶች ሪፖርትን ጥራቱን፣ ወቅቱንና ተከታታይነቱን ጠብቆ በተሟላ መረጃ አስደግፎ ያለመላክ፤ የተለያዩ የምርት ግብዓቶችን ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ እጥረት ማጋጠሙ፤ የአሲዳማ አፈር ለማከም ኖራ ለማቅረብ የበጀት እጥረት መከሰቱ፤ የፀጥታ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች በመስክ በመገኘት አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ አለማድረግ ተጠቃሽ መሆናቸውን አመላክተዋል:: በመሆኑም እንደተግዳሮት የተነሱት እነዚህ አብይ ችግሮችን ለመፍታት ሚኒስቴሩ በቀጣዩ ስድስት ወራት ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ ነው የተናገሩት::

ተቋሙን የገመገመው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ግብርና ሚኒስቴር የግብርናው ትርንስፎርሜሽን ለማረጋገጥና ዘርፉን ለመደገፍ ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት የሀገርን ምርት እና ምርታማነት ለማሻሻል የተያዘውን ጥረት የበለጠ ማጠናከር እንደሚገባ አሳስቧል:: የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ፤ የምግብ ዋስትናን ለመረጋገጥ የግብርና ዘርፉን በቴክኖሎጂ ማዘመን እንደሚገባ፣ አሲዳም አፈርን ለማከም አስፈላጊ የሆኑ የኖራ ግብዓቶችን በማቅረብ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን በመቅረፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት አስገንዝበዋል::

ማህበራዊ

# አስኳላ

## ዳግም ወደ ተግባር የገባው ማዕከል

**ግርማ መንግሥቴ**

ይህቺ "ዳግም"የምትባል ቃል በአንድ ወቅት የወቅቱን የቃላት ገበያ ምንዛሪ ተቆጣጥራ እንደነበር ይታወሳል። በተለይ ወደ ትምህርት ሚኒስቴርና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (የግል) አካባቢ የዘወትር ፀሎት እስከ መሆን ደርሳ እንደነበር ሁላችንም፣ ለአቅመ ማወቅ የደረስን ሁሉ እናስታውሳለን።

በተለይም በዘጠናዎቹ መጨረሻና በሚሌኒየሙ መግቢያ አካባቢ የእንትና ኮሌጅ "ዳግም እውቅና አገኘ"፤ እንቶኔ ዩኒቨርሲቲ "የዳግም እውቅና ፍቃድ ተሰጠው"፤ "እንትና ሕንፃ ሦስተኛ ፎቅ ላይ ሦስት ክፍሎችን ተከራይቶ 'እንትና ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት' በሚል ስያሜ ተማሪዎችን ተቀብሎ ሲያስተምር የነበረው ተቋም ተነጥቆ የነበረው ፍቃዱ ተመልሶለት ዳግም እውቅናን በማግኘት ወደ ሥራ ገብቷል"(ይህ ባለ ሀበት "ልጆቹ ስፖርት የሚሰሩት የቱ ጋ ነው?"ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ፣ "እሱን እያሰብንበት ነው"ሲል የሰጠው መልስ እስከ ዛሬም ድረስ ብዙዎችን እንዳሳቀ ነው።)

መቼም የትምህርትን ነገር ትምህርት ያነሳዋልና ነው እንጂ ከላይ ያሉትን ወደ ማስታወስ ያዘገምነው የዛሬዋ "ዳግም"ከእነዛኛዎቹ "ዳግሞች"ጋር የምትገናኝ ሆና አይደለም። "ይገናኛሉ"ማለት ግድ ከሆነ እንኳን፣ በአንድ ወቅት ታግደው የነበሩ መሆናቸው ሲሆን፤ በማን?፣ ለምን?፣ እንዴት? ወዘተ በሚለው ይለያያሉና ግንኙነታቸው ከሴማንቲክስ የሚያልፍ አይሆንም።

ዳግም ወደ ተግባር ወደ ገባው፣ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል ከመሄዳችን በፊት ስለ ባህል ማዕከላት፤ ወይም የባህል ማዕከላትና የትምህርት ተቋማት ትስስር አንዳንድ ሃሳቦችን እናንሳ።

በግልፅ እንደሚታወቀው ሁለቱም ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው። ሁለቱም የማንነት መገለጫዎች ሲሆኑ፤ ሁለቱም የእውቀት ምንጮች፣ ሁለቱም ማኅበራዊ ተሳትፎን ግድ የሚሉ ናቸው።

የባህል ማዕከላትና የትምህርት ተቋማት ተመጋጋቢዎች ሲሆኑ፤ ሁለቱም ተደጋጋፊዎች ናቸው። ሁለቱም ሀገር እንደ ሀገር እንዲቆምም ሆነ ሀገር እንደ ሀገር ሆኖ ወደ ፊት እንዲራመድ አስፈላጊዎች ሲሆኑ፤ ሁለቱም የአንድ ሀገር የወደ ፊት አዝማሚያ ጠቋሚዎች ናቸው። ባይሆኑ ኖሮ ባህላዊ እውቀት፤ ባህላዊ ትምህርት፤ ባህላዊ መድኃኒት፤ ባህላዊ እሴት (ቁሳዊም፣ መንፈሳዊም)፤ ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ወዘተ ይሉ ጉዳዮች ባልኖሩም ነበር።

ባህል የማንነት መገለጫ ባይሆን ኖሮ እነ "ሄቦ"(በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ማኅበረሰቦች አንዱ የየም ማኅበረሰብ ዘመን መለወጫን የሚቀበልበት፤ ግጭት የሚፈታበት፣ ሰላም የሚሰፍንበት፤ እንዲሁም በድብቅ የተሠሩ ወንጀሎች የሚጋለጡበት ሥርዓት) ባልነበሩም ነበር፤ ባህል፣ ሳይንስ . . . አንድነት፣ ትስስር፣ ተደጋጋፊነት ወዘተ ባይኖራቸው ኖሮ እነ ዩኔስኮ (የመጀመሪያዋ አባልና፤ ከአፍሪካ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ ቀዳሚዋ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ 195 አባል ሀገራት ያሉት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት)ን የመሳሰሉ ግዙፍ ዓለም አቀፍ ተቋማት ባልተፈጠሩም ነበር። ወደ ሀገራችን ስንመጣም ያውና ተመሳሳይ ነው።

ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በስሩ በሚገኘው የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል አማካኝነት ሰኔ 2010 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ "የባህል ማዕከላት ሚና ለኢትዮጵያዊነት ግንባታ" እና "በኢትዮጵያዊነት ፊልሞች ውስጥ ኢትጵያዊነት አለን?" በሚል ርእስ ለሁለት ቀናት የቆየ ውይይት አካሂዶ ነበር። በውይይቱም በርካታ ጥናቶች የቀረቡ ሲሆን፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ታድመው ነበር።

ከጥናት አቅራቢዎቹ አንዱም ሠዓሊና ቀራፂ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥነ ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት መምህር የሆኑት ተባባሪ ፕሮፌሰር በቀለ መኮንን ሲሆኑ፣ "የባህል ማዕከላት የሰው ልጅ የፈጠራ ጥበባት መለማመጃ ቦታዎች በመሆናቸው፤ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ ማንኛውም ዜጋ ሊጠቀምባቸው መቻል አለበት። ይህም ተግባራዊ መሆን ሲጀምርና የባህል ማዕከሉ በመደበኛነት ሁሉንም ማገልገል ሲጀምር የሚጠበቀውን ማየት እንጀምራለን"በማለት ነበር የባህል ማዕከላትን አስፈላጊነት ያስረዱት።

በዚሁ መድረክ ለአንድ ሀገር ሕዝቦች የባህል እና የኪነ ጥበብ እድገት የባህል ማዕከላት ሚና ከፍተኛ



መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል ዋና ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ሽመልስ "የአንድ ሀገር የባህል ማዕከል የሕዝቦቿ የባህላቸው ውጤት በመሆናቸው በተለይም እንደ እኛ ሀገር ብዝሃ ባህል ያለን ሕዝቦች ስንሆን የባህል ማዕከላት ሚና ላቅ ያለ ነው። በመሆኑም በዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ እንዲህ ያሉ ውይይቶችን ከባለድርሻ አካላት ጋር መወያየቱ ጠቃሚ ነው"በማለት መናገራቸው፤ የወቅቱ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትር ወይዘሮ ፎዚያ አሚን በበኩላቸው፤ "የሀገር ግንባታ በብዙ አስተሳሰቦች፣ እውቀቶችና ጥረቶች የሚመጣ ነው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል አዘጋጅነት የሚደረገው ይህ ውይይት እንደ ፌዴራል ተቋም ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ጉዳዮች ለመሥራት የጀመርነው እንቅስቃሴ ማሳያ ነው"ማለታቸው በወቅቱ ሰፊ የመገናኛ ብዙኃንን ሽፋን ማግኘቱ ይታወሳል።

በመሆኑም፣ ባህልን፣ ትምህርትን፤ እንዲሁም፣ የባህል ማዕከላትን እና የትምህርት ተቋማትን ነጣጥሎ ማየት ከመክሰር ያለፈ ትርፍ የለውም ማለት ይሆናል።

ለመግቢያ ያህል ይህንን ካልን ወደ አአዩ ባህል ማዕከል እንመለስ። ማለትም:-

"በተማሪዎች ጥያቄ በኪነ ጥበብ አፍቃሪያን ውትወታና በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቀና ትብብር ባለፈው ኅዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም አንጋፋ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ አርቲስቶችና የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በተገኙበት ከአሥር ዓመት መዘጋት በኋላ ዳግም ወደ ሥራ መመለሱ ይፋ ተደርጓል፡፡"የሚል ዜና ተነግሮለት ወደ ነበረው፤ ወደ ሥራ ከተመለሰ በኋላ ከጥር 8 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ልዩ የሆነ የኪነ ጥበብ መሰናዶ ማቅረብ ወደ ጀመረው (ተማሪዎች ግጥሞችን፣ ተውኔቶችንና ሙዚቃን እያዘጋጁ ለታዳሚዎች በማቅረብ ላይ ወዳሉበት)፤ በሀገሪቱ ኪነጥበብ ታሪክ ውስጥ ዘመን የማይሽረው መሠረትን ወደ ተከለው፣ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል (በቀድሞ ስሙ የአፄ ኃይለሥላሴ የባህል ማዕከል) ዳግም ወደ ተግባር መመለስ እንመለስ።

የሀገሪቱን ባህልና ጥበብ ከማበልፀግ አንፃር ከፍተኛ ሚናን ሲጫወትና የድርሻውን ሲወጣ የነበረው የአአዩ ባህል ማዕከል ታሪክ እንደሚያስረዳው፣ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም መጋዘን የነበረን ቤት ወደ አዳራሽነት በመቀየር የባህል ማዕከሉን ማቋቋም ተቻለ። ምክንያቱ ደግሞ በወቅቱ በሀገሪቱ የነበሩ የኪነ-ጥበብ ተቋማት ከቁጥር የማይገቡ ስለነበሩ፤ የባህል ማዕከሉ መቋቋም፤ በዩኒቨርሲቲውና ከዩኒቨርሲቲው ውጪ የሚገኘውን ማኅበረሰብ ከጥበብ ማዕድ ተቋዳሽ ማድረግን መነሻ ያደረገ ነው።

ቀድሞ በባህል እና ኪነጥበባዊ ቅርሶች ጥበቃ እና ስነዳ ዙሪያ በርካታ ሥራዎችን ይሠራል ተብሎ በሚጠበቀው የባህል ማዕከል ሲንቀሳቀሱ ከነበሩ የጥበብ ሰዎች (Alumni) መካከል በርካታ ለሀገርም፣ ለዓለሙም የተረፉና አንቱ የተባሉ የኪ(ሥ)ነጥበብ ሰዎች ያሉ ሲሆን፣ ዐሻራቸውም በባህል ማዕከሉ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

"በዚህ አንጋፋ የጥበብ ማዕከል ከዚህ በፊት እነ ማን ነበሩ?"የሚል ጥያቄ ለሚያነሱ የጥበብ ቤተሰቦችም መልስ ያለ ሲሆን፣ እንደ ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ተስፋዬ እሸቱ ማብራሪያ "የጋሽ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ የጋሽ አባተ መኩሪያ፣ የጋሽ ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር፣ የጋሽ ዮሐንስ አድማሱ፣ የጋሽ መንግሥቱ ለማ ቤት ነበር።"

ከሰሞኑ፣ ማዕከሉን ከተመለከቱ ዐቢይት ጉዳዮች መካከልም አንዱ እና ምናልባትም ዋና ሆኖ ሲሰማ የነበረው "ማዕከሉ ከመቼውም በላይ የራሱን ዐሻራ ለማሳረፍ ቤቱን ወለል አድርጎ እየጠበቃችሁ ነው። ደራሲያን ኑ፤ ድርሰታችሁን አቅርቡ፤ ፀሐፊያንም ፃፉ፤ አዘጋጆችም ቴአትራችሁን አዘጋጁ፤ መለማመጃ ስፍራ አጥታችሁ በየቦታው ያላችሁ የኪነ ጥበብ አፍቃሪያንና አማተር ተዋንያን እባካችሁ ኑ፤ ማዕከሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ ክፍት ነው"የሚለው የዋና ዳይሬክተሩ ጥሪ ሲሆን፤ ብዙዎችም ጥሪውን በደስታ እንደተቀበሉት ለሚዲያ ሲሰጡት ከነበረው አስተያየት ለማወቅ ተችሏል።

ይህ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰርከስ ማኅበር ጥምረት ጋር በጋራ መሥራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ሥምምነት የተፈራረመው (ኅዳር 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ከኢትዮጵያ ሰርከስ ማኅበር ጋር በመሆን ታላቅ የኪነ ጥበብ ምሽት አድርጓል) የአአዩ ባህል ማዕከል፣ ልክ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ በ"ሐዲስ ዓለማየሁ የባህል እና የምርምር ተቋም"አማካኝነት፣ "ኢትዮጵያ ያላት ጥንታዊ የታሪክ፣ ሥነጥበብ፣ የእምነት፣ የሥልጣኔ፣ የሥነጽሕፈት፣ ኅብር ያለው የብሔር ብሔረሰቦች ባህል፣ ሀገር-በቀል ዕውቀት፣ የሥነጽሑፍ እና የሥነ ዜማ ቅርስ፣ የሕዝቡ ማኅበራዊ አኗኗር፣ ወዘተ በአግባቡ እንዲጠና፣ ዕውቅና እንዲያገኝ፣ እንዲደነቅ እና ከዘመናዊ ሥርዓተ ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ ለመማር ማስተማሩ ሒደት አገልግሎት"መስጠት ላይ እየሠራሁ ነው እያለ እንዳለው ሁሉ፤ እንደ እናት ዩኒቨርሲቲነቱ የበለጠ ይሠራል ተብሎ ይጠበቃልና ይህንንም ከዚሁ ጋር ሰንቆ ሊሄድ ይገባል።

"በባህል፣ በሥነ ጥበብ፣ በቋንቋ፣ በሥነጽሑፍ፣ በቅርጻ ቅርጽ፣ በቤተ መዘክር (ሙዚዬም)፣ በሥነ-ሙዚቃ፣ በግዕዝ ምርምር ዘርፎች ላይ ፍላጎቱ፣ ችሎታው እና ሙያዊ ክሂሎቱ ላላቸው የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አባላትና ለአካባቢው ሕዝብ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችን"መስጠትን ዓላማው አድርጎ እንደ ተነሳው ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ (በጉዳዩ ላይ እየተጋ ያለውን፣ ወሎ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ)፣ አአዩም የበለጠ በማድረግ ይወጣዋል የሚለው የብዙዎች አስተያየት ነው። የባህል እና የሥነጥበብ ቅርስ ጥበቃ እና ስነዳንም በተመለከተ እንደዚያው።

የኅብረ-ባህል (የሰው ልጆችን ሁሉ የጋራ ቅርስ የያዘ) መገለጫ የሆኑት የባህል ማዕከላት፣ በተለይም የከፍተኛ ትምህርት የባህል ማዕከላት ለከፋ የፖለቲካ ሽመታ መሣሪያ (አንዳንድ ጸሐፍት "የፖለቲካል ቁስ"ሲሉ ነው የሚገልጿቸው) እና ለእርስ በእርስ ግጭት የዋሉትን፣ "ባህል"እና "ቋንቋ"ን መሠረት ያደረጉ ግንዛቤዎችን ለኅብረተሰቡ በማስጨበጥ ሁሉም አደብ እንዲገዛና ወደ ቀልቡ እንዲመለስ በማድረግ በኩል የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ከዚህ በመለስ የሚባል አይደለም። ከዚህ አኳያ የአአዩ የባህል ማዕከልም በዚሁና ሌሎች መሰል ተግባራቱ ብዙዎችን ወደ ቀልባቸው ይመልሳል ተብሎ ይጠበቃል።

ወደ ፊት በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ታሪክ ብቻ ሳይሆን በዓለምአቀፍ ደረጃ በፈጠራ ሥራዎቻቸው፣ በዲፕሎማሲ ችሎታቸው፣ በሀገር አስተዳደር ብቃታቸው፣ በጦር ሜዳ ውሎና የአርበኝነነት ተጋድሏቸው እጅግ ከፍተኛ ክብር፣ አበርክቶ ያላቸውና ስመ ገናና ሰብዕናዎች ስምና ሥራዎቻቸው ይነሱበታል ተብሎ የሚጠበቀው የአአዩ የባህል ማዕከል በጀትና የሰው ኃይሉ በይፋ ተወስዶበት ተቋማዊ ማንነቱ በጠራራ ፀሐይ ተነጥቆበት አመታትን ቢያስቆጥርም (መቼም ግፍ ነው የተሠራው)፤ ከዚያ ሁሉ በማገገም፣ በፍጥነት ወደ ነበረበት በመመለስ ታሪክ እንደሚሠራ ቀደም ሲል በማዕከሉ ያገለገሉ ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም የጥበብ፣ ባህል፣ እውቀትና እውነት አድናቂዎች ሁሉ ተስፋና ምኞት ነው።

የዩኒቨርሲቲው ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ እንደሚሉት የባህል ማዕከሉ በኪነ ጥበብ ዘርፍ ዘመን ተሻጋሪና የማይረሱ ሥራዎችን በማከናወን አስተዋጽኦው የላቀ ነው።

በ1956 ዓ.ም የተቋቋመውና በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ የኪነ-ጥበብ ማሰልጠኛ ማዕከል መሆኑ የሚነገርለት ማዕከሉ የኪነ-ጥበብ ሥራዎች ባልተስፋፉበት ጊዜ ድንቅ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን ያኖረ መሆኑን ያስታወሱት ተጠባባቂ ፕሬዚዳንቱ፥ የማዕከሉን የኪነ-ጥበብ ምሽቶች እንደገና ማስጀመሩ ለዘርፉ እድገት ትልቅ ትርጉም አለው ብለዋል።

የባህል ማዕከሉ በሀገሪቱ በርካታ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በማፍራት ባለውለታ መሆኑን፤ ከሌሎች የኪነ ጥበብ መፍለቂያዎች የሚለየው ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ባለተሰጥኦዎች ገጣሚዎች፣ ዘፋኞችና ሌሎችም የኪነ ጥበብ ዝንባሌ ያላቸው ተማሪዎች በኅብረት የሚገኙበት መሆኑን የሚናገሩት የባህል ማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ተስፋዬ እሸቱ (ረዳት ፕሮፌሰር) እንደሚናገሩት ከሆነ፣ በማዕከሉ የሚቀርበው ሳምንታዊ ፕሮግራም በጉጉት የሚጠብቁትና የሚናፍቁት ምሽት እየሆነ መጥቷል።

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስመጥር እንዲሆን ካደረጉት ተቋማት መካከል ፈር ቀዳጁ የባህል ማዕከሉ ነው የሚሉት ዋና ዳይሬክተር ተስፋዬ እሸቱ ለዘርፉ እድገት አሁንም የራሱን ዐሻራ በማኖር አስተዋጽኦ ለማድረግ በየሳምንቱ ማክሰኞ፣ ሐሙስና ቅዳሜ ፊልም የሚያሳይ ሲሆን በቀረቡት ፊልሞች ላይ በወር አንድ ጊዜ ውይይት ይደረጋል።

በማዕከሉ በቋሚነት የሚስተናገዱ ፕሮግራሞች ያሉ ሲሆን፣ አንዱም «የአንድ ግጥም የአንድ ወግ እንግዳ» የሚለውና፣ አንጋፋ የኪነ ጥበብ ሰዎች በየሳምንቱ የሚጋበዙበት፣ እውቅ አርቲስቶች ሥራቸውን የሚያቀርቡበት ፕሮግራም እንደሆነ ከኃላፊዎቹ ማብራሪያዎችና ካለፉት ፕሮግራሞች ለማወቅ ተችሏል። ከሰላሳ በላይ ባሉ የዩኒቨርሲቲ ባህል ማዕከላት የሚገኙ ተማሪዎች በአንድነት ሆነው የየራሳቸውን ሥራዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተሰባስበው የሚያቀርቡበት ፌስቲቫል እንዳለም እንደዚያው።

እስካሁን ባለው ሁኔታ፣ ታዋቂ የኪነጥበብ ሰዎች (አዜብ ወርቁ፣ ገነት ንጋቱ፣ ግሩም ዘነበ፣ ጎሳዬ ተስፋዬ፣ ሰለሞን ቦጋለ እና ሌሎችም) "የአንድ ግጥም የአንድ ወግ እንግዳ"በሚለው የወሩ የኪነ ጥበብ ምሽት መድረክ ላይ በመገኘት ሙያዊ ምክርና አስተያየታቸውን የሰጡ መሆኑን ከባህል ማዕከሉ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ሪፖርተር ጋዜጣ እንደዘገበው፣ የአዲስ አበባ የተማሪዎችና የአስተዳደር ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አብዱራዛቅ መሃመድ (ዶ/ር) በመድረኩ ባደረጉት ንግግር፣ በኢትዮጵያ መደበኛ የባህል ፖሊሲ ከመርቀቁ በፊት ሀገራዊ ውክልና ያለው ተቋም እንደሆነ መስክረዋል፡፡ ፈር ያለው የቋንቋ ፖሊሲ ከመታሰቡ በፊት የቋንቋዎች እኩልነት ሲቀነቀንበት የነበረ፣ የሐሳብ እኩልነትና ነፃነት እምብርት ከመሆኑ ባሻገር፣ መልክ ያለው የኪነ ጥበብ እንቅስቃሴ ከመስፋፋቱ በፊት ተፅዕኖ ፈጣሪ ጠቢባን ያፈራ የባህል ማዕከል መሆኑንም በደማቁ አስምረውበታል።

እንደ ዶ/ር አብዱራዛቅ የወቅቱ ንግግር ማዕከሉ ሀገራዊ እሴቶችን ከፍ የሚያደርጉ፣ የትውልድን አካዳሚያዊና ሥነ ምግባራዊ ሰብዕና የሚያድሱና የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚያላብሱ፣ ልዩነትን በወል እሴቶች የሚያስተሳስሩ፣ እያዝናኑ የሚያስተምሩ ሀገራዊ ግጥሞች፣ መዝሙሮች፣ ሙዚቃዎችና ቴአትሮች ሲቀርቡበት ቆይተዋል። አሁንም አድማሱን በማስፋት በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ ለመሆን እየሠራ ይገኛል፤ በሂደትም ወደ ዓለም አቀፍ መድረኮች።

በቅርቡ በሀገራችን የመጀመሪያው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የሆነው፤ ለብዙ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች መነሻ በመሆን ለበርካታ አሠርት አመታት የኪነ ጥበብ መፍለቂያ የሆነው፤ ለኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከተው፤ ዕውቅ ከያኒያን የማይፋቅ ዐሻራቸውን ያሳረፉበት፤ ከ"እንኳን ደስ አላችሁ!!!"ጀምሮ የማይደበዝዝ ትዝታቸውን ያኖሩበት የአአዩ ባህል ማዕከል ዳግም ወደ ሕይወት፤ ካለ መኖር ወደ መኖር እንዲመጣ ላደረጉት ሁሉ ምስጋናችንን እያቀረብን "ከባህል ማዕከሉ ጋር ወደ ፊት!!!"በማለት የዛሬውን ዝግጅታችንን እናጠቃልላለን።

# ወቅታዊ

# "የኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ በየትኛውም መመዘኛ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚደግፈው ነው"

- አቶ ሙሉአለም ኃይለማርያም
የዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር

በሰጥሻቸው ልዑልሰገድ እና መክሊት ወንድወሰን

ቀይ ባህር በአፍሪካ እና በእስያ መካከል የሚገኝ የውሃ አካል ሲሆን ትልቅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ጂኦሎጂካል ጠቀሜታ አለው። ባህሩ በምዕራብ ከግብፅ፣ በምሥራቅ ሳውዲ አረቢያ እና በደቡባዊ ሱዳን ይዋሰናል ይህም ለንግድ እና ወታደራዊ እንቅስቃሴ ስትራቴጂካዊ ቦታ ያደርገዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እንደ ሳውዲ አረቢያ እና ኢራን ያሉ ሀገራት በቀጣናው ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር ስለሚፎካከሩ የቀይ ባህር የጂኦፖለቲካዊ ውጥረቶች ማዕከል ሆኗል። ባሕሩ በየቀኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የነዳጅ በርሜሎች ማስተላለፊያ መንገድም ነው።

ቀይ ባህር ከፖለቲካዊ ጠቀሜታው በተጨማሪ የተፈጥሮ ሀብትና የብዝሀ ህይወት ባለቤት ነው። ባህሩም ለዘመናት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል። ለኢትዮጵያ ወሳኝ የንግድ መስመር ሆኖ ከዓለም ጋር በማገናኘት ወደ ሀገር ውስጥ እንድታስገባ እና ወደ ውጭ እንድትልክ ለዘመናት ሲያስችላት ቆይቷል።

በወቅቱ ኢትዮጵያ የአክሱም መንግሥት በመባል ትታወቅ የነበረች ሲሆን በአካባቢው ትልቅ የንግድ ኃይል ነበራት:: ሀገሪቷም በቀይ ባህር አቅራቢያ በመገኘቷ በአፍሪካ፣ በአረብ እና በህንድ መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ለመቆጣጠር አስችሏት ቆይቷል::

በቀይ ባህር ላይ የአክሱም ስርወ መንግሥት የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ፣ ቅመማ ቅመም፣ ጨርቃጨርቅ እና የተለያዩ ሸቀጦችን ይገበያይ ነበር። በእስላማዊው ወርቃማ ዘመን (Islamic Golden Age) ቀይ ባህር ለሙስሊም ነጋዴዎች ጠቃሚ የንግድ መስመር ሆኖ ነበር። የኢትዮጵያ ነጋዴዎችም እንደ እጣንና ከርቤ ያሉ ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ በንግዱ ተሳትፈዋል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓ ኃያላን በቀይ ባህር አካባቢ ፍላጎት ማሳየት ጀመሩ:: ኢትዮጵያ ባላት ስልታዊ አቀማመጥ እና ቅኝ ካልተገዙ ሁለት የአፍሪካ ሀገራት አንዷ በመሆኗ የአውሮፓ ትኩረት ሆነች። እንደ እንግሊዝ እና ጣልያን ያሉ የአውሮፓ ኃያላን በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር እና የቀይ ባህርን ተደራሽነት ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ ጀመሩ።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ የቀይ ባህር መዳረሻ በኢትዮጵያና በኤርትራ ጦርነት ወቅት አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ ነበር። የኢትዮጵያ ግዛት ስር የነበረችው ኤርትራ በሕዝበ ውሳኔ በግንቦት 16፣ 1985 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ነጻ መውጣቷን ተከትሎ፤ በቀይ ባህር የሚገኘውን የአሰብ ወደብን ተቆጣጠረች። ይህም ኢትዮጵያ በቀጥታ የባህር መዳረሻ እንዳትሆን አድርጓል።

ዛሬ ኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም ጋር በምታደርገው የንግድ ልውውጥ የጅቡቲ ወደብ ትጠቀማለች። ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ቀጥተኛ መዳረሻ ባይኖራትም አሁንም የቀጣናው ጠቃሚ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ አጋር ናት።

በፖለቲካው ኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች የባህር መዳረሻዋን ለማስፋት ስትፈልግ ቆይታለች። ከእነዚህ መንገዶች አንዱ እንደ ጅቡቲ እና ሶማሌላንድ ባሉ የጎረቤት ሀገራት ወደቦች ማልማት ነው። እነዚህ ወደቦች ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ተጠቃሚ እንድትሆን ከማድረጉም በላይ ሸቀጣ ሸቀጦችን ወደ ውጭ እንድትልክ እና እንድታስገባ አስችሏታል።

በኢኮኖሚ ዘርፍ ቀይ ባህር ለኢትዮጵያ ጠቃሚ የንግድ መስመር ነው። ባህሩ በኢትዮጵያ እና በተቀረው ዓለም መካከል ወሳኝ የሆነ ትስስር በመፍጠር እቃዎቿን ወደ ውጭ እንድትልክ እና አስፈላጊ ግብዓቶችን እንድታስገባ ያስችላታል። በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያ ቀይ ባህር ታሪካዊ መዳረሻዋ ቢሆንም እንደቀደምት ተጠቃሚነቷ ተገቢውን አገልግሎት ማግኘት አልቻለችም:: ለዚህም ማሳያው ኢትዮጵያ 95 በመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን የንግድ ልውውጥ የምታስተናግደው በጅቡቲ ወደብ ላይ በእጅጉ ጥገኛ በመሆን ነው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ለ30 ዓመታት በቀይ ባህር ጉዳይ የበይ ተመልካች ሆና ቆይታለች::

አሁን ግን ሀገሪቱ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጨምረውን የሕዝብ ቁጥርና የገቢ እና ወጪ ንግድ ለማሳለጥ በለውጡ መንግሥት በቀጣናው የባህር በር ጥያቄ ተነስቷል:: በዛሬው ወቅታዊ አምዳችን የቀይ ባህር እና የባህር በር ጥያቄን



አስመልክቶ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ከሆኑት አቶ ሙሉአለም ኃይለማርያም ጋር ቆይታ አድርገናል::

**አዲስ ዘመን፡- የባህር በርን አስመልክቶ ዓለም አቀፍ የውሃ ሕግ ምን ይላል?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** ዓለም አቀፍ የውሃ ሕግ ድንበር ተሻጋሪ ለሆኑ የውሃ አካላት የራሱ የሆነ ሕግ አስቀምጧል:: ነገር ግን ባህር ከአንድ ሀገር ወደሌላ ሀገር የሚፈስ ወይም የሚንቀሳቀስ አይደለም:: ቢሆንም ድንበር ተሻጋሪ ያልሆኑ የውሃ አካላትን የምንጠቀምበት መንገድ(ሜካኒዝም) አለው:: ለመጓጓዣ(ናቪጌሽን) እና ለምርምር(ለኤክስፕሎሬሽ) አገልግሎት ሲሆን የራሱ የሆነ በኪሎ ሜትር የተወሰነ የአጠቃቀም ሥርዓት አለው:: ነገር ግን ለባህር በር አገልግሎት ሲሆን ዩናይትድ ኔሽን ኮንቬንሽ ኦን ዘ ሎው ኦፍ ዘ ሲ(united nation convention on the law of the sea) በ1983 የወጣ እና እስካሁንም በአገልግሎት ላይ ያለ ስምምነት ተግባራዊ ይደረጋል:: ይህ ኮንቬንሽን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በምን አግባብ የባህር በር መጠቀም እንደሚችሉ ይደነግጋል:: ነገር ግን ይህ ሕግ ፍጹማዊ(አብሶሊዩት) የማይለወጥ ሕግ አይደለም::

ኢትዮጵያ እና ሌሎች እንደኢትዮጵያ ያሉ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር በር ለማግኘት የሚያስችላቸው ሶስት መንገዶች አሉ::

የመጀመሪያው፤ ከዚህ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ በሰቶ መቀበል ሕግ ነው:: ይህም ሲባል ቀላል አይደለም ሰጥቶ ለመቀበል ኢትዮጵያ ካሏት ሀብቶች ውስጥ የህዳሴው ግድብን፤ የእርሻ መሬትን፤ ቴሌኮምን፤ አየር መንገድ የመሳሰሉ ሀብቶችን የተወሰነ ድርሻ ሰጥቶ በምትኩ ወደብ ማግኘት የሚል ነው::

ሁለተኛው፤ ከሌሎች ሀገራት ጋር በመሆን ወደብን በማልማት መጠቀም ነው:: ለምሳሌ ብናነሳ የበርበራ ወደብ 19 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ አልምቶ የመጠቀም ስምምነትን ማንሳት እንችላለን:: ሶስተኛው እና የመጨረሻው አማራጭ በኃይል የወደብ ፍላጎትን ማሳካት የሚል ነው:: የዓለም አቀፍ ሕግም የሚለው ይህንን ነው ::

**አዲስ ዘመን፡- ሀገራችን የባህር በር እንድታገኝ የሚደግፉ የሕግ ማእቀፎች አሉ?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** በዓለም አቀፍ ደረጃ ከዩናይትድ ኔሽን ኮንቬንሽ ኦን ዘ ሎው ኦፍ ዘ ሲ (united nation convention on the law of the sea) በኋላ ብዙም ስለወደብ የሚያወሩ የሕግ ማእቀፎች አልወጡም:: ሆኖም ግን በየቀጣናው የሚወጡ ሕጎች አሉ:: እነዚህ ሕጎችም ቢሆኑ ይህንን የባህር በር እከሌ ለሚባል ሀገር ስጡ የሚል አይደለም:: በትብብርና በጋራ በመሆን ወደብን በማልማት እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ነው::

ለኢትዮጵያ ይህንን ያህል በመቶ ከቀይ ባህር ላይ ትውሰድ የሚል ሕግ የለም:: ነገር ግን ኢትዮጵያ በታሪክ የምታነሳቸው ጥያቄዎች አሉ:: ኢትዮጵያ እስከ የመን ድረስ ግዛቷ የነበረ ቢሆንም፤ ዓለማችን በየእለቱ ተቀያያሪ በመሆኗ አሁን የባህር በር የሌላት ሀገር ሆናለች:: ነገር ግን አሁንም ያበቃለት ነገር አይደለም በሚቀጥሉት ጊዜያት ልናገኝ የምንችልባቸው እድሎች አሉ፤ የተዘጋ ነገር አይደለም::

ሕጉ የሚደግፈው ከኤርትራ ⍰ ከጅቡቲ ጋር በትብብር እንድንሰራ ነው:: ይህንን ለማድረግ ጠንከር ያሉ የዲፕሎማሲ ስራዎች ይጠይቃሉ:: ኢትዮጵያ በዚህኛው አካሄድ እንደ አዲስ ወደብ የምታገኝበት ሳይሆን ከዚህ ቀደም የነበራትን ወደብ የምትጠይቅበት ነው:: በኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ ውስጥ የወደብ ባለቤት የነበረች ሀገር ናት::

ኢትዮጵያ በታሪኳ ወደብ ያጣችው ኤርትራ በጣሊያን ቀኝ ግዛት ውስጥ በነበረችበት ጊዜ እና ኢህአዴግ ወደ ስልጣን በመጣበት ወቅት ነበር:: ስለዚህ ያሉት ህጎች በግድ ወይም በሃይል የሚባለውን ነገር የሚደግፉ ሳይሆኑ በጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ እና በሰቶ መቀበል መርህ ወደብ እንድታገኝ የሚደግፉ ናቸው::

**አዲስ ዘመን፡- የባህር በርን በሰላማዊ መንገድ እንድናገኝ ምን አይነት የዲፕሎማሲ ስራዎች መሰራት አለባቸው?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** ኢትዮጵያ የባህር በር የምታገኝባቸው እድሎች አሉ:: ከ1890 እስከ 1940 ኤርትራ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ስር ነበረች:: ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ኤርትራ በሪፈረንደም ከኢትዮጵያ ጋር እንድትዋሃድ ማድረግ ችለዋል:: ይህ የዲፕሎማሲ ሥራም ኤርትራና ሕዝቦቿን ከመመለስ ባሻገር ኢትዮጵያ የባህር በር እንድናገኝ አድርጓታል:: በዚህ ሂደት ውስጥ ጦር አልተማዘዙም:: ሂደቱን ማሳካት የቻሉት በሁለት መንገድ ነበር:: አንደኛው ከኤርትራ ሕዝቦች ጋር ባለን የታሪክ እና የባህል ቁርኝት በመጠቀም ሲሆን፤ በዚህ ሂደት ውስጥ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ አጼ ምኒልክ ኤርትራን ለጣሊያን ትቷታል በሚል ያኮረፉ አካላትን የማስማማት ሥራ ተሠርቷል:: በሌላ በኩል አንድ ሕዝቦች ነን በደም የተሳሰርን ነን የሚሉ ወገኖች በመኖራቸው ያንን ተጠቅመው ሪፈረንደሙን ማሳካት ችለው ነበር::

ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በወቅቱ ከነበሩ ኃያላን ሀገራት ጋር ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጠንካራ የሆነ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ኤርትራን የኢትዮጵያ አንድ ግዛት ማድረግ ችለዋል:: በ1950ዎቹ እንግሊዝ ኢትዮጵያን በመርዳት ከጣሊያን ቅኝ ግዛት ማስለቀቅ ስለቻለች ኤርትራን ለመልቀቅ ለበርካታ ዓመታት ፍላጎት አልነበራትም:: ነገር ግን በመጨረሻ በጠንካራ ዲፕሎማሲ ኤርትራ የኢትዮጵያ አንድ አካል ሆነች:: በዚህም አጥታ የነበረውን የባህር በር ማስመለስ ችላ ነበር::

አሁንም ኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎቷን በሁለት መንገድ ማሳካት ትችላለች:: የመጀመሪያው ከሚመለከታቸው ሀገራት ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በመሥራት ሲሆን፤ በተለይም በቀጣናው የባህር በር ካላቸው ሀገራት ጋር ማለትም ከኤርትራ፤ ከጅቡቲ እና ከሱማሊያ ጋር ጠንካራ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ ትብብር መፍጠር አስፈላጊ ነው:: ጎረቤታችን ከሆነችው ኤርትራ ጋር የምጽዋን እና የአሰብን ወደብ ለመጠቀም ቅርብ በመሆኗ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎች መሥራት ይጠበቅብናል::

በኤርትራ በኩል የማይሳካ ከሆነ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ያስፈልጋል:: ለሰጥቶ መቀበል መርሁ መሳካት እጅግ አጓጊ ነገሮችን ይዞ መቅረብ ያስፈልጋል:: ይህ ዓይነቱ አካሄድ ዓመታትን ሊወስድ ይችላል:: ለምሳሌ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ጊዜ የነበረው የባህር በር የማስመለስ ሂደት በአጠቃላይ ለ10 ዓመታት የቀረበ ጊዜን የወሰደ ነበር::

እንደበርበራ ያሉ ወደቦችን የማልማት ሂደትም ጠቃሚ ነው:: ይህንንም ለማሳካት ዲፕሎማቶች ብቻ ሳይሆኑ መንግሥታትም ጭምር ትኩረት ሰጥተው ሊጓዙበት ይገባል:: ተደጋጋሚ ጉብኝቶችን እና ውይይቶችንም ማድረግ ጉዳዩን ሊያፈጥነው ይችላል:: በተጨማሪም ኃያላን ሀገራትን ማነጋገር ያስፈልጋል:: በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ ሀገራት የሆነ ነገር ሰጥተው በምትኩ ሌላ ነገር በመቀበል ነው የሚሰሩት፤ በመሆኑም ኃያላን ሀገራት በቀጣናው ላይ ያላቸውን ፍላጎት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ውይይቶች እና የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መስራት ይኖርብናል::

ከዓለም አቀፍ ተቋማት እና ሀገራት ጋር በትብብር መስራትና ሰጥቶ የመቀበል ፖሊሲን መከተል ቅድሚያ ልንሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: ይህም አስፈላጊ የሆነው ኢትዮጵያ የባህር በር እንድታገኝ ዓለም አቀፍ ተቋማት ድጋፍ እንዲያደርጉላት ለማስቻል ነው:: ይህንን ማድረግ ከተቻለ ኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎቷን የማሟላቷ ነገር በሰላማዊ መንገድ እውን መሆን ይችላል::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የባህር በር ያላት ሀገር መሆኗ ይታወቃል:: በታሪክ አጋጣሚ የባህር በር ኖሯቸው የማያውቁ በመሬት የተከበቡ ሀገራት የባህር በር ካላቸው ሀገራት ጋር ያላቸው የግንኙነት ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** በታሪክ አጋጣሚ የባህር በር ኖሯቸው የማያውቁ ሀገራት የባህር በር ካላቸው ሀገራት ጋር ያላቸው ግንኙነት ለወደብ በሚከፍሉት ዓመታዊ የገንዘብ ክፍያ ላይ የተመሰረተ ነው:: ልክ አሁን ኢትዮጵያ ለጅቡቲ እንደምትከፍለው ማለት ነው:: ነገር ግን በአፍሪካ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# "የኢትዮጵያ የወደብ ጥያቄ በየትኛውም...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

እና በሳውዝ አሜሪካን ያሉ አንዳንድ ሀገራት በአቅራቢያቸው ከሚገኙ የባህር በር ካላቸው ሀገራት በሰጥቶ መቀበል መርህ የባህር በር ፍላጎታቸውን ሊያሳኩ የቻሉ አሉ።

ኢትዮጵያ የባህር በር ቢኖራት በቀይ ባህር ጉዳይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራት ከማድረግ ባለፈ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቷ እና የውጭ ኢንቨስተሮችን ቁጥር የመጨመር እድሏን እጅግ ከፍ ያደርገዋል። ፖለቲካዊ ተሰሚነቷን እና የደህንነቷን(security) ጉዳይም ታጠናክራለች።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ኢትዮጵያ ያነሳችው የባህር በር ጥያቄ ምን ያህል ተገቢ ነው?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** በአሁኑ ሰዓት አየሩን ከያዙ ነገሮች መካከል የኢትዮጵያን የባህር በር ጥያቄ ዋጋ የሌለው አድርጎ የማየት ነገር ነው። በየማህበራዊ ሚዲያው ብንመለከት የኢትዮጵያን የባህር በር ተገቢነት የሌለው አድርገው የሚመለከቱ በርካታ ሰዎችን እናያለን፤ ይህ ትክክል አይደለም። የኢትዮጵያ የባህር በር ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመጡ በኋላ የተነሳ ጥያቄ አድርጎ የሚያስብ ሰውም አለ። መሬት ላይ ያለው ሀቅ ግን በመንግሥታት ለውጥ ውስጥ ኢትዮጵያ የባህር በር ባልነበራት ጊዜያት ውስጥ ሁሉ ሲጠየቅ የነበረ ጥያቄ መሆኑ ነው።

በተለይም 1890 በኋላ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በdomestic politics ትልቅ ቦታ አላቸው የሚባሉት አፄ ምኒልክ ወደ ደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ያደረጉት ዘመቻ አላማው ሰዎችን ግብር አስገብሮ ለማዕከላዊ መንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ አልነበረም። አንዱ አላማቸው የዛን ጊዜዋን ዜይላ የአሁኗን ጅቡቲ መቆጣጠርና የኢትዮጵያ አካል ማድረግ ነበር፤ ባይሳካላቸውም። ስለዚህ ምኒልክ ጦር ጭምር አዝምተው ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን ጥረት አድርገዋል።

ቀጥሎ የመጣው ልጅ እያሱም ሕፃን ቢሆንም ስለሱ የተፃፉ ፅሁፎችን ብንመለከት 'አንድ ቀን ግመሎቼ የቀይ ባህርን ውሃ ይጠጣሉ' ይል እንደነበር እናያለን። ንግግሩ ውስጥ ምኞት እንደነበረው መመልከት እንችላለን፤ የባህር በር ጥያቄ ነበረ ነው።

ኤርትራ እና ኢትዮጵያ ከተቀላቀሉ በኋላ ከEPLF (Eritrean people liberation front) ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል ያደረጉት ለሁለት ምክንያቶች ነበር። ግዛታዊ አንድነቱን ማስጠበቅ(ሉአላዊነትን ማስከበር) እና ኤርትራ ከተገነጠለች ወደብ እናጣለን የሚል ስጋትም ስለነበር ነው። የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም ወደ ስልጣን ከመጡ በኋላ ሳይደረግ ይቆይ በሚል እንጂ ጉዳዩ አይነሳም ብለው አላሰቡም ነበር። ቀጥለው የመጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝም አንዱ አጀንዳቸው ይሄው የወደብ ጉዳይ ነበር። እንዳሁኑ ጎልቶ በየሚዲያው አይወጣም እንጂ የባህር በር ጥያቄ ኢትዮጵያ የባህር በር ባጣችባቸው ጊዜያት ሁሉ በመንግሥታት ለውጥ ውስጥ የነበረ ትልቅ ጥያቄ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በቴሌቪዥን መስኮቶች መጥተው ሃሳቡን ከማንሳታቸው በፊት የባህር በር ሳይኖረን የባህር ኃይል አደራጅተናል። ይህ ተግባራቸው ወደፊት የባህር በር ሊኖረን ይችላል የሚል ነው።

አሁን ባለንበት ጊዜ ሊበራል የሆነው ዓለም ስለበዛ፣ ነጻ ገበያ የበላይነቱን ስለያዘ፣ ትልልቅ ኢንቨስተሮች ከሀገር ወደ ሀገር እየሄዱ ኢንቨስት የሚያደርጉበት ጊዜ ከመሆኑ የተነሳ የባህር በር ቢኖረን በኢኮኖሚው ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ የወጣቱን የማህበረሰብ ክፍል ፍላጎትና የሥራ እድል ጥያቄ ሊያቀዘቅዝልን የሚችል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል። ስለዚህ የባህር በር ጥያቄው ተገቢ ነው ወይ? አዎ ተገቢ ነው። ከኢኮኖሚ፣ ከፖለቲካ እንዲሁም ከደህንነትም አንፃር ካየነው ጥያቄው ተገቢ ነው የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም በባህር በር በኩል የራሳችን ድርሻ ሊኖረን ይገባል። እድሉ ኖሮን የባህር በር ጥያቄያችን ቢመለስልን በዚህ ምክንያት ብቻ አብረውን ሊሰሩ የሚችሉ በርካታ ኃያላን ሀገራት እንደሚኖሩ አልጠራጠርም።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ የባሕር በር ጥያቄ በዚህ ወቅት መነሳቱ ተገቢ ነው?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** የግብርና፣ የትምህርት እና የጤና ፖሊሲ ብለን እንደምናወጣው የውጭ ፖሊሲም አንዱ የፐብሊክ ፖሊሲ አካል ነው። ስለባህር በር ስናወራ ስለውጭ ፖሊሲ እያወራን ነው። ሀገሪቱ የውስጥ ችግሮች ስላሉባት የግብርና፣ የትምህርት እና የጤና ፖሊሲ ተግባራዊ መደረጉን አላቆመም።

በእርግጥ በውጭ ፖሊሲ ይሄ ተገቢ ጊዜ ነው፤ ይሄ ተገቢ ጊዜ አይደለም የሚባሉ ነገሮች አሉ። በኔ እምነት ግን ጉዳዩን አነሳን ማለት በኃይል እናሳካለን ማለት አይደለም። በኃይል እናሳካለን የሚል ነገር በሌለበት ዛሬም ነገም ጉዳዩን በየቀኑ ትኩረት ሰጥተን እያነሳን ብንሄድ ስህተት የለውም ባይ ነኝ።

የባህር በር ጥያቄው ጊዜው አይደለም ለሚሉ ሰዎች፤ ትምህርት አላቆምንም፤ ጤና አገልግሎት አላቆምንም፤ በግብርናው ዘርፍም ቢሆን ምርት ማምረት አላቆምንም። ይሄም አንድ እንደ ውጭ ፖሊሲ መርህ የማናቆመው ዛሬም ነገም የምናነሳው ጉዳይ ስለሆነ ጥያቄው መነሳቱ ተገቢ ነው፤ ወቅታዊ ጉዳይም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ ቀደም ወደነበሩ ዘመናት እንመለስና ኢትዮጵያ የባህር በር በነበራት ወቅት የነበረችበት ከፍታና የባህር በር ካጣች በኋላ ያለችበትን ሁኔታ በንፅፅር እንዴት ልንገልፀው እንችላለን?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** የባህር በር በነበረን ጊዜ የሚያዳምጠን ብዙ ነው። በቀጥታ ተሳትፎ የምናደርግባቸው ጉዳዮች ብዙ ነበሩ።

ቀይ ባህር የዓለማችን 10 በመቶ የንግድ የባህር ላይ ንግድ የሚካሄድበት ቦታ ነው። ቀይ ባህር ላይ በዋናነት ንግድ የምናከናውነው እኛ አይደለንም። በአብዛኛው ንግዱን የሚያከናውኑት ትልልቆቹ ሀገራት ናቸው። ቀይ ባህር ኢዥያን ከአፍሪካ፤ አፍሪካን ከአውሮፓ የሚያገናኝ ትልቅ የውሃ አካል ነው። ስለዚህ የቀይ ባህር ወደብ ባለቤት በሆንን ቁጥር እነዚህ ኃያላን ሀገራት ጭምር የየራሳቸው ፍላጎት ስላላቸው እና አካባቢው ሰላማዊ እንዲሆን ስለሚፈልጉ ከኛ ጋር ይሰራሉ።

የቀይ ባህር ባለቤት በነበርንባቸው ጊዜያት ሁሉ ካለን ሀብት ካለን ታሪክ በቅኝ ያልተገዛን ከመሆናችን የተነሳ በቅርብ ኢትዮጵያ ጋር የሚሰሩ የዓለም ሀገራት እና የዓለም አቀፍ ተቋማት ቁጥር ከፍተኛ ነበር። የቀይ ባህር ባለቤትነታችንን ካጣን በኋላስ የሚለውን ስንመለከት ግን በቀይ ባህር ጉዳይ ኢትዮጵያን የሚጋብዝ አካል የለም።

ከኢኮኖሚ አንፃር፤ በተለይ ቀዝቃዛው ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ የሊበራል አይዶሎጂ አብላጫውን ቦታ በመያዙ ሁሉም ሀገራትን የውጭ ኢንቨስትመንትን ወደ ሀገር መሳብ(come and invest) የሚለው ሃሳብ እየተስፋፋ መጣ። ከዛ በፊት እኛ ሀገር የምትከተለው የሶሻሊዝም አይዶሎጂ ስለነበር የመንግሥት ሀብት እንጂ የግል ሀብት ማፍራት የሚደገፍ ባለመሆኑ መንገዶች ሁሉ ዝግ ነበሩ። በመሆኑም ለኢንቨስትመት ምቹ አልነበረም። ቢያስን ግን ለሌሎች ሀገራት የምሸጣቸው የተወሰኑ ምርቶቻችንን በጅቡቲ ወደብ በኩል የገንዘብ ክፍያ እየከፈልን እንልክ ነበር። አሁንም በዚህ መልኩ በመጠቀም ላይ እንገኛለን።

የቀይ ባህር ባለቤት በነበርን ሰዓት ለጅቡቲ ወደብ የምንከፍለውን ገንዘብ ለልማት እናውለው ነበር። አሁን የቀይ ባህር ባለቤት ባልሆንበት ወቅት ደግሞ ለጅቡቲ ወደብ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር እየከፈልን እንገኛለን። ይህ ብቻም አይደለም፤ ገጠር የሚኖረው አብዛኛው ሰው የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ ሳንችል ለጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል ሰጥተናል። ይሄ ሁሉ የሚደረገው ጅቡቲ አኩርፋ የባህር በር እንዳትከለክለን ነው።

በፖለቲካው ዘርፍም ቢሆን የባህር በር ስለሌለን ተሳትፏችን ተገድቧል። በሆነ ሳጥን ውስጥ የተገደብን እንድንሆን አድርጎናል። ወደኋላ መለስ ብለን ብንመለከት የኢትዮጵያ ድንበር የት ድረስ ነበር አሁንስ የት ነው ያለው የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። የባህር በሮቻችንን የማንለቅባቸው እድሎች ነበሩን ግን አባክነናቸዋል። ወደፊት እንደምንም ብለን መልሰን የምናገኝበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል ብዬ አስባለው።

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ግንኙነትን ከማጠናከር አንፃር አሁን ላይ ምን መሠራት አለበት?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** ቀይ ባህር ላይ ቀጥተኛ ድርሻ ካላቸው ጎረቤት ሀገራት ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት አለብን። ወዳጅነታችንን እያጠናከርን መሄድ ያስፈልጋል። ክፍተቶቻችንን እየሞላን መሄድ ይኖርብናል። በአፍሪካ ካሉ ሀገራት በተጨማሪ ከአረብ ሀገራት ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር አለብን። ወደኋላ ተመልሰን ብንመለከት ከአረብ ሀገራት ጋር የነበረን ግንኙነት ባለመተማመን ላይ የተመሰረተ ነበር።

አረብ ሀገራት ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑ ቡድኖችን ይደግፋሉ የሚል ክስ ላለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ መንግሥታት ይነሳ ነበር። ነገር ግን በተለይ የኢህአዴግ መንግሥት ከመጣ በኋላ፤ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመጡ በኋላ ከአረብ ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት በአንፃራዊነት ወደመተማመን ደረጃ ከፍ እያለ በመሆኑ ከነሱ ጋር መሥራት ያስፈልጋል።

ይህንን የምልበት ምክንያት ለምሳሌ የኤርትራን መንግሥት ብንመለከት ወደ አሜሪካ ሀገራት ጉብኝት



አያደርግም፤ ወደ አብዛኞች የአውሮፓ ሀገራት እንዳይገባ ተከልክሏል። ቢሄድ ሊሄድ የሚችለው ወደ ሩሲያ ነው። የአረብ ሀገራት ግን ብዙ ተመላልሶ የሚሄድባቸው ሀገራት ናቸው። ስለዚህ ከነሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ባጠናከርን ቁጥር የኤርትራን መንግሥት የሚያሳምኑበት እድል ሰፊ ስለሆነ ከአረብ ሀገራትም ሆነ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- ይህን ሁሉ ርቀት ተሄዶ የወደብ ጥያቄው ባይሳካ ምን መደረግ አለበት?**

**አቶ ሙሉአለም፡-** ለወደብ ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ የማግኘት እድል ሃምሳ ሃምሳ ነው። የወደብ ጥያቄው ስለተነሳ ብቻ ይሳካል ማለት አይደለም። ለዚህ ጥያቄ በአዎንታዊ ምላሽ ለማግኘት ዓመታትን ሊፈጅ ይችላል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድሮ የወደብ ጥያቄ ስላነሱ ዘንድሮ ይሳካል ማለት አይደለም። ለሚቀጥሉት 10 ዓመታትም ላይሳካ ይችላል። ምክንያቱም ጠንካራ የሆነ ዲፕሎማሲና እርስ በእርስ መተማመን ከሚጠይቁ ዘርፎች መካከል አንዱ ነው።

ጥያቄያችን ባይሳካ አሁን እየተከተልን ያለነውን መንገድ አጠናክረን መቀጠል አለብን የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን አይሳካም መንገዱ ዝግ ነው የሚባል ነገር ስለሌለ ጥያቄያችንን በተገቢው መልኩ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል። ባይሳካም ለጊዜው አልተሳካም ብሎ ማለፍና እንደአዲስ መሞከር እንጂ እስከመጨረሻው ተስፋ ቆርጦ መተው መፍትሄ አይሆንም።

ከዚህ ቀደም ጠቅላይ ሚኒስትሩም እንደተናገሩት፤ እንደሀገር ወደብ ማግኘት ለኛ እጅግ ወሳኝ ነው። ተሳክቶልን በሰጥቶ መቀበል መርህ ወደብ ማግኘት ብንችል ስኬታማ እንሆናለን። 30 በመቶ የህዳሴ ግድብን እንዲያስተዳድሩ ተደርጎ ወደብ ማግኘት ቢቻል ጥቅሙ ያመዝናል። መለያችን የሆነውን አየር መንገድ የተወሰነውን ፐርሰንት ቢጋሩና ለኛ የባህር በር ቢሰጡን ይሄም አዋጭ ነው። ያለምንም ግጭት ምንም አይነት የህይወት ዋጋ ሳንከፍል የባህር በር ለማግኘት ከመሞከር ለኛ በምንም ያዋጣናል። የእርሻ መሬት ሰጥተን የባህር በር ማግኘት በራሱ ለኛ አዋጭ ነው።

ወደ ጦርነት መጥተን በጉልበት የባህር በር እናግኘው ብንል ግን ብዙ ዋጋ ሊያስከፍለን የሚችል ነገር ነው። እንደመጨረሻ አማራጭ ልንከተለው እንችላለን፤ ነገር ግን ያዋጣናል ወይ የሚለውን ማየት ያስፈልጋል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አጥተን የባህር በር ብናገኝ ለቀጣዩ ትውልድ ሊጠቅም ይችላል፤ ነገር ግን ይህ ነገር ምን ያህል ያዋጣል? በጦርነት ተሸንፎ የባህር በር የሰጠው አካልስ ነገ ኃይሉን አደራጅቶ ተመልሶ ለመልስ ምት አለመምጣቱን እርግጠኛ ነን ወይ? ለቀጣዩ ትውልድስ ያለው የዲፕሎማሲ ሥራ ከባድ አይሆንበትም ወይ የሚሉትን ጉዳዮች ማሰብ አስፈላጊ ነው።

በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ ሁልጊዜ በቋሚነት ኃይል ይዞ መቆየት ላይኖር ይችላል። ዛሬ ከፍተኛ ኃይል ያለው ሀገር ነገ በሌላ ጉልበተኛ ኃይሉን ሊነጠቅ የሚችልባቸው እድሎች ሰፊ ናቸው። በመሆኑም በኃይል የሚገኝ የትኛውንም ነገር ዘላቂነቱን መተማመን አንችልም። በጊዜውም አንፃር በኃይል ነገሮችን ማድረግ እኛን የሚመጥነን ተግባር አይደለም። ጊዜው ነገሮች በንግግር ተግባብቶ የሚከናወኑበት ነው።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የሴቶች መዋቢያ ‹‹ሜክ አፕ›› በባለሙያዎች እይታ

**ሰሚራ በርሀ**

ለውበት መጨነቅ ፣ ቆዳን መንከባከብ የሚባሉ ርዕሶች በቀጥታ ከሴቶች ጋር የሚገናኙ ይመስላል:: እንደ ሀገራችን ባህልም ብዙ አይነት መዋቢያዎች ሴቶች በቤታቸው ቆዳቸውን የሚንከባከቡባቸው የሚያሳምሩባቸው በውበታቸው ጎልተው እንዲታዩ የሚያደርጉባቸው ልማዶች ብዙ ናቸው:: ታዲያ ሰለጠነ በምንለው ዓለም በውበት አጠባበቅ ዙሪያ ላይ የሚሰጡ አይነታቸውም ብዙ ነው:: በርካታ ባለሙያዎችም ይገኛሉ:: ሴቶችም በቤታቸው ከሚያደርጓቸው ልማዶች ባለፈ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ከትናንሽ የውበት ሳሎኖች ወደ ትልልቅ የውበት ሳሎኖች በማምራት የቆዳቸውን ንጽህናና ውበት ይጠብቃሉ::

ራስን የማስዋብ ነገር ሲነሳ አሁን ባለንበት ዘመን በተለይ ሴቶች ቆዳቸውን ለመንከባከብና አምረው ለመታየት በዘመናዊ መንገድ የተሰሩ ምርቶችን ይጠቀማሉ:: በባለሙያዎች እና በተጠቃሚዎች ዘንድ ውበትን ያጎላል የሚባልለት በሌሎች ጎራ ደግሞ ራስን ይቀይራል ሰዎች በራሳቸው ውበት እንደማይተማመኑ ማሳያ ነው የሚባልለት ‹‹ ሜክ አፕ ›› ወይንም በገጽ ላይ የሚቀቡ ምርቶችን መጠቀም እየተለመደ መጥቷል::

በሀገራችን እነዚህን መዋቢያ ምርቶች የሚጠቀሙ ሴቶችም እየተበራከቱ መጥተዋል:: በተመሳሳይ አገልግሎቱን የሚሰጡ የውበት ሳሎኖችም በየሕንጻዎቹ በዝተው ይታያሉ:: በዛሬው የፋሽን ገጻችን እነዚህን የገጸ ቅብ መዋቢያ ምርቶቸ ለሽያጭ ከሚያቀርቡ እና በውበት ሳሎን ውስጥ አገልግሎቱን ከሚሰጡ ባለሙያዎች ጋር ቆይታ አድርገናል::

‹‹ኤምኬ የውበት ሳሎን›› በመሀል አራት ኪሎ አምባሳደር የገበያ አዳራሽ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፤ የሜክ አፕ ባለሙያዋ ቅድስት ሙሉነህ የጥፍር ሥራ ሜክ አፕ እና ሌሎች አገልግሎቶችን በውበት ሳሎኗ ትሰጣለች:: ሙያውን ከልጅነቷ ጀምሮ ትወደው የነበረ በመሆኑ በኋላ በትምህርት የተደገፈ ስልጠናን በመውሰድ የራሷን የውበት ሳሎን ከፍታ አገልግሎቱን እየሰጠች ነው:: ከዚህ ቀደም በነበራት ልምድ እንስቶች ስለ ሜክ አፕ የነበራቸው እውቀት እምብዛም አልነበረም ፤ መሰራት ሲፈልጉም ውስን ለሆኑ ፕሮግራሞች



በባለሙያዎች ምርጫ ይሰራሉ:: ‹‹አሁን ላይ ሜክ አፕ የሚሰሩ ደንበኞቻችን በብዛት መሰራት የሚፈልጉትን አይነት ጠንቅቀው የሚያውቁ ናቸው›› በማለትም ግንዛቤው እየተሻሻለ ምምጣቱን ታነሳለች።

የውበት ሳሎኑ መስራች ቅድስት እንደምትለው እንስቶቹ የሚጠቀሙት የመዋቢያ መሳሪያዎች እንደየቆዳ ቀለማቸውና የቆዳቸው አይነት ደረቅ፣ ወዛም ተብሎ ይለያል:: ምርቶቹ ውበትን የሚያላብሱ ቢሆንም ፊታችን ጥርት ያለ ለመሆን መዋቢያ ምርቶቹ የሚያመጡትን ውጤት እንደሚቀንሰው ቅድስት ትናገራለች::

ደንበኞቿ ወደ ኤምኬ የውበት ሳሎን የሚመጡት ጥሪዎች ሲኖሩባቸው አልያም የእርግዝና ጊዜያቸውን በፎቶ ማስቀረት ሲፈልጉ መሆኑን ትናገራለች:: የሠርግ ሥነ-ሥርዓቷን የምታካሂድ ሙሽሪት ከሆነች ደግሞ ደንበኞቿ ወደሚገኙበት ቦታ የመስሪያ እቃዎቿን ይዛ በመሄድ ከነ ሚዜዎቿ አገልግሎቱን ትሰጣለች:: ደንበኞቿ ሜክአፕ ለመሰራት ወደ እሷ ሲመጡ በመጀመሪያ የቆዳ አይነታቸውን በመጠየቅ ያላቸውን የቆዳ ቀለም በማየት የሚስማማውን ምርት ታዘጋጅላቸዋለች፤ ፊታቸውን በሚስማማቸው መታጠቢያ ማጽዳት የመጀመሪያው ሥራ ነው ::

አንድ ሙሉ ሜክ አፕ ለመስራት የሚያገለግሉ ግብዓቶች ከ10 በላይ መሆናቸውን የምታነሳው ቅድስት ቀለል ያለ ሜክ አፕ ለመስራት ግን ውስን ግብዓችን እንደምትጠቀም ትገልፃለች:: በሙያው ረጅም ጊዜ የቆየችው ቅድስት ከዚህ ቀደም የነበረው ፋሽን ቀጭን ቅንድብ፣ ጎላ ብለው የሚታዩ የተለያየ ቀለም ያላቸው የዓይን ሻዶው እና ደማቅ የከንፈር ቀለም (ሊፒስቲክ ) ነበር :: ነገር ግን በአሁን ሰዓት የምርቶቹ መሻሻል የፋሽን መለዋወጥ ሰዎች በአብዛኛው መሰራት የሚፈልጉት ፍፁም ከቆዳ ቀለማቸው ጋር ተመሳሳይ የሆነ እና ተፈጥሯዊ ውበታቸውን የሚያጎላ የሜክ አፕ አይነት ነው:: የአንድ የሜክ አፕ ባለሙያ ችሎታው የሚለካውም በእንስቷ አይን ላይ የሚጠቀማቸው ምርቶች መጠንና ጠንቃቃ መሆን እንደሆነ ቅድስት ጠቅሳለች ::

ቅድስት ቀለል ያለ ሜክአፕ ሰርቶ ለማጠናቀቅ ከ45 ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት የሚወስድባት ሲሆን፤ የሙሽሮችና የሚዜዎች ከሆነ ደግሞ እስከ አንድ ሰዓት ተኩል ጊዜን ይወስዳል :: ለዚህም ደግሞ ቀለል ያለ ሜክ አፕ ለሚሰሩ ደንበኞች ከሁለት ሺህ ብር ጀምሮ ለሙሽሮች እስከ 10 ሺህ ብር የሚደርስ ክፍያ ትጠይቃለች:: ዋጋውም እንደስራው እና እንደየውበት ሳሎኑ ይለያያል :: ሜክአፕ ራሱን የቻለ ጥበብና ውበት ይኑረው እንጂ ቅድስት ሜክ አፕ የተሰሩ እንስቶች ማታ ሳያስለቅቁት በፍጹም መተኛት እንደሌለባቸው ገልጻለች:: ዘርፉ በርካታ የሥራ እድልን እየፈጠረ በመሆኑ ሙያውን የሚስተምሩ ትምህርት ቤቶች ተበራክተው ይገኛሉ::

የመዋቢያ ምርቶች በአጠቃላይ ከተለያዩ ሀገራት የሚገቡ ሲሆን፤ ጊዜያቸው ያላለፈባቸው ምርቶች መሆናቸውን ማጣራትም መረሳት የሌለበት ጉዳይ መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ:: ታዲያ እነዚህ ምርቶች እያስመጡ የሚያቀርቡ እንዳሉ ሁሉ በሀገራችን የተሰራ ምርት ማቅረብ የጀመረ ‹‹ሄላዝ ቢውቲ ››የሚባል ካምፓኒ አለ። የተለያዩ የመዋቢያ ምርቶችን የሚያቀርብ ሲሆን፤ ለየት የሚያደርገውም ለኢትዮጵያውያን እና ለአፍሪካውያን ቆዳ ተብለው የተሰሩ ምርቶችን ማቅረቡ እንደሆነ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

የሜክ አፕ ባለሙያዋ አብሳላት አበራ የዚህ ሀሳብ ተጋሪ ነች። ‹‹ከውጭ የመጡ መዋቢያዎችን በምንጠቀምበት ወቅት የተለያየ ቁጥር ያላቸውን ምርቶች ቀላቅለን ለመጠቀም እንገደዳለን ፤ ሄላዝ ግን ለኛ ቆዳ ተብሎ የተሰራ በመሆኑ እንደዛ ማድረግ አይጠበቅብንም›› ትላለች:: በሄላዝ ቢውቲ የሚገኙ አስፈላጊ የሚባሉ መዋቢያዎች ሲሆኑ የከንፈር ቀለም፣ ፋውንዴሽን ፣ ኮንሲለር ፣ ፓውደር ሁሉም ምርቶች ይቀርባሉ:: ምርቶቹም ሀገር በቀል በመሆናቸው ኢትዮጵያዊ ስሞችን ይዘዋል ‹‹ውቢት ፣ በርቺ ፣ ደፋር ፣ ጀግኒት›› እንዲሁም የተለያየ ስሞች፣ የወራት ስያሜዎች ከመስከረም እስከ ጳጉሜ የተሰየሙ ሀገራዊ ስያሜዎችን የያዙ ምርቶችን ያቀርባሉ:: እነዚህን ምርቶች በአብዛኛው ለመግዛት የሚመጡት ሴቶች ሲሆኑ በጥቂቱ ስጦታ መስጠት የሚፈልጉ ወንዶችም ለመግዛት ወደ ሱቁ ይመጣሉ::

የውበት አጠባበቅ ባለሙያዎች ሜክ አፕ መጠቀም ላይ የተለያየ መክረ ሀሳብ የሚሰጡ ሲሆን፤ ሁሉም ግን ባእድ ምርቶችን በፊት ቆዳ ላይ በምንጠቀምበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ። ለምርቶቹ አዲስ የሆኑ ተጠቃሚዎችም በቆዳቸው ላይ ከማድረጋቸው በፊት ባለሙያዎችን እንዲያማክሩ ያሳስባሉ።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የተሽከርካሪ ብክነት እና የትራንስፖርት ችግር

**ዋስልኝ አየለ**

ልብ ብላችሁ ከሆነ አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ይላሉ:: ‹‹ምናባቱ ደግሞ ለመንግሥት ገንዘብ!›› የራሴ አይደለም አይቆጨኝም እንደማለት ነው:: አንድ ሰው የግሉን ነገር ሲያባክን ሲያስተውሉ ‹‹የመንግሥት ንብረት አደረከው እኮ!›› ይላሉ:: በጥንቃቄ ያዘው ማለታቸው ነው፤ የመንግሥት ከሆነ ግን ቢባክንም ችግር የለውም እንደማለት ነው:: ብዙ ሰዎች በቤታቸው የማያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት የመንግሥት ተቋም ውስጥ ነው:: ውሃ ሳይዘጉ መሄድ፣ የኤሌክትሪክ ገመዶችን እና ማከፋፈያዎችን ማበላሸት፣ በር በኃይል መወርወር፣ የበር እጀታ መገንጠል... እነዚህን እና የመሳሰሉት መረን የለቀቁ ግዴለሽነቶች የሚደረጉት በመንግሥት ተቋም ውስጥ ነው:: የቤቱን ዕቃዎች ግን በጥንቃቄ ይይዛቸዋል:: በዚህ ሁኔታ ብዙ የመንግሥት ንብረት ይባክናል፤ ሕዝብ ግን በአገልግሎት ይቸገራል::

የአዲስ አበባ የትራንስፖርት ችግር እንኳን ነዋሪው አዲስ አበባን የረገጠ ሁሉ የሚያውቀው ነው:: በትራንስፖርት ምክንያት ብዙ ጊዜ ይባክናል:: የአንድ የታክሲ ሰልፍ ርዝመት ከአንድ የታክሲ ፌርማታ አያንስም:: የመጨረሻው ሰልፍ ጋር ለመድረስ ታክሲ ያስፈልጋል እየተባለ ሁሉ ይቀለዳል::

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በትንሽ ብልሽት ምክንያት አገልግሎት አቁመው የሚባክኑ ብዙ ተሽከርካሪዎች አሉ:: በመንግሥት ተቋም ግቢ ውስጥ ብዙ ተሽከርካሪዎችን ታያላችሁ:: ከእነዚያ ውስጥ ግን ምናልባትም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አገልግሎት የማይሰጡ ናቸው:: በአንድ ትንሽ ብልሽት ምክንያት ቆመው ሙሉ ለሙሉ ለመበላሸት የተዘጋጁ ናቸው:: ፀሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው በአቧራና ጭቃ የዛጉ ናቸው:: በትንሽ ብር ይስተካከል የነበረው ችግር ባለመስተካከሉ በሚሊዮን የተገዛ ተሽከርካሪ ከጥቅም ውጪ ይሆናል ማለት ነው::

**የመንግሥት** ንብረት ሲባል የሕዝብ ንብረት ማለት ነው:: እነዚያ በግዴለሽነት የምናበላሻቸው መገልገያዎች በከፈል ግብር የተገዙ ናቸው

ችግራቸው በጣም ቀላል መሆኑን የነገረኝ በተከራየሁበት ግቢ ውስጥ ያለ አንድ የአንበሳ አውቶቡስ አሽከርካሪ ነው:: ከከባድ ተሽከርካሪዎች እስከ ትንንሽ ተሽከርካሪዎች በትንሽ ብልሽት ምክንያት ሥራ ያቆሙ ብዙ ናቸው:: አሽከርካሪው እንደ ባለሙያ ስለሚያውቀው አንዳንዶቹ በቀላሉ ችግራቸው አንድ ሰዓት እንኳን የማይወስድ፣ አምስት ሺህ ብር እንኳን ወጪ የማያስወጣ መሆኑን ታዝቧል:: በትንሽ ችግር ምክንያት ሥራ ያቆመ ተሽከርካሪ እያለ ተቋሙ ግን ለአንዳንድ ሥራዎች ብዙ ወጪ አውጥቶ ኮንትራት ይዋዋላል:: ወይም በውድ ዋጋ ሌላ ተሽከርካሪ ይገዛል:: ወይም ከዛሬ ነገ በሚል ቸልተኝነት የሥራ መስተጓጎል ይፈጠራል:: የተሽከርካሪው ችግር ግን ምናልባትም ጎማ መቀየር ሊሆን ይችላል::

የትራንስፖርት ችግርን ለመቅረፍ ተብሎ ብዙ አይነት አማራጮች ሲነገሩ እንሰማለን:: አሁን ባለው የምንዛሪ ውድነት ከፍተኛ ወጪ ወጥቶ ተሽከርካሪዎች ይገዛሉ:: ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በጥቂት ወጪ መስተካከል የሚችሉት ተሽከርካሪዎች ላይ ትኩረት አይደረግም:: የማሽን ዕቃ ነውና አገልግሎት ሳይሰጥ በቆየ ቁጥር እየዛገ እና የበለጠ እየተበላሸ ይሄዳል:: በዚህም ምክንያት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ይሆናሉ::

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢቢሲ) ከሦስት ዓመት በፊት በሠራው ዘገባ፤ ተበላሽተው የቆሙና መወገድ ያለባቸው ከሁለት ሺህ በላይ ተሽከርካሪዎች በመንግሥት ተቋማት ተገኝተዋል:: ሌሎች የንብረት አይነቶችም ተበላሽተው መወገድ እንደሚገባቸው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ አስታውቋል:: በዚያው ዘገባ ውስጥ፤ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ሐጂ ኢብሳ በንብረት ምዝገባው በብልሽት ምክንያት የቆሙና ሊወገዱ የሚገባቸው 2 ሺህ ተሽከርካሪዎች ውስጥ በቀላል ጥገና የሚሰሩ አሉበት ብለዋል:: ይሄ ማለት እንግዲህ ብዙ ክትትል ቢደረግ በየመሥሪያ ቤቱ ሥራ አቁመው ፀሐይና ዝናብ ከሚፈራረቅባቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ በቀላል ጥገና አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ ማለት ነው::

በወቅቱ በተደረገው የምዝገባ ሂደት፤ 200 የሚጠጉ ማሽነሪዎች፣ 700 ሺህ ኪሎ ግራም ቁርጥራጭ ብረቶች፣ 40 ሞተር ብስክሌቶች እና ሌሎች ንብረቶች መገኘታቸው ይፋ ተደርጎ ነበር::

እንግዲህ ምን ያህል ንብረት እንደሚባክን ልብ በሉ:: ይህ በአንድ ሪፖርት ወይም በአንድ ቃለ መጠይቅ (ለዚያውም ከሦስት ዓመት በፊት) የተገኘ ብቻ ነው:: የተበላሹት ተሽከርካሪዎች ተሽጠው የሚያስገኙት ገቢ ይኖር ይሆናል:: ዳሩ ግን ተበላሽተው ሲሸጡ ከሚያስገኙት ገቢ ቀላሉን ብልሽት በማስተካከል የሚሰጡት አገልግሎት ይበልጥ ነበር:: ሲበላሹ ንብረትነታቸው ብቻ አይደለም መታየት ያለበት:: አንድ ተሽከርካሪ ሲበላሽ የተገዛበት ዋጋ ሳይሆን መታየት ያለበት ይሰጠው በነበረው አገልግሎት ያጣነውን ጥቅም ነው:: በትራንስፖርት ችግር ምክንያት የባከነውን ጊዜ እና የሰው ኃይል ነው ማሰብ ያለብን:: ሥራ ላይ ከሚውለው ጊዜ ይልቅ ለትራንስፖርት ሰልፍ የሚውለው ጊዜ ሊበልጥ ነው ማለት ነው::

ይህ በተሽከርካሪ ብቻ የታዘብነው ነው:: ሌሎች የመንግሥት ተቋም ንብረቶችን ልብ በሉ:: ከጠረጴዛ እና ወንበር እስከ ትልልቅ ንብረቶች በጥንቃቄ ጉድለት ይበላሻል፤ በዚያው ይባክናል:: የመንግሥት ንብረት ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ብዙ ሰው በግዴለሽነት ይጠቀምበታል:: ቤታችን ውስጥ ላለው ወንበር ወይም መስታወት የምናደርገውን ጥንቃቄ መሥሪያ ቤታችን ውስጥ ላለው ወንበር ወይም መስታወት ጥንቃቄ አናደርግም:: ይህ እጅግ ሲበዛ ኋላቀርነት ነው::

የመንግሥት ንብረት ሲባል ግን የማን ይሆን? ይህንን እንኳን ማሰብ የተሳነን ነን:: የመንግሥት ንብረት ሲባል የሕዝብ ንብረት ማለት ነው:: እነዚያ በግዴለሽነት የምናበላሻቸው መገልገያዎች በከፈል ግብር የተገዙ ናቸው:: ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚበጀተው በጀት የሕዝብ ገንዘብ ነው:: የመንግሥት ገንዘብ ሲባል ከየት የሚመጣ እየመሰለን ይሆን?

እንደ ሕዝብ ይህ የግንዛቤ ችግር አለ:: እንደ መንግሥት ደግሞ እጅግ ሲበዛ ግዴለሽነት ይታያል:: ከፍተኛ ቁጥጥርና ክትትል የለም:: ለምሳሌ፤ አንድ የፌዴራል ተቋም ተበላሽተው የቆሙ ተሽከርካሪዎች አሉት እንበል:: የተቋሙ አመራሮች ምን ሆነው እንደቆሙ ለምን አይጠይቁም? እንደ ችግሩ መጠን ለምን እንዲስተካከል አያደርጉም? በአንዲት ትንሽ ችግር የቆመ መኪና ሲኖር እንዴት አይቆጫቸውም?

አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣን ወይም የመንግሥት ተቋም፤ ለሌላው ሕዝብና ተቋም አርዓያ ነው መሆን ያለበት:: የዝርክርክነት እና የብክነት ምሳሌ መሆን የለበትም:: የግዴለሽነት እና የምን አገባኝነት ስሜት የሚንፀባረቅበት መሆን የለበትም:: የተበላሹ እና የቆሸሹ ነገሮች የሚታዩበት መሆን የለበትም:: ለሀገርና ለሕዝብ ኃላፊነትን የመወጣት ተምሳሌት መሆን ነው የሚገባው:: ለዚህ ደግሞ ተራው ሠራተኛም ሆነ ከፍተኛ ኃላፊዎች በኃላፊነትና በተቆርቋሪነት ሊሠሩ ይገባል!

## ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያን ስጋት ግልፅ ያደረገው ዓለም አቀፋዊ ቀውስ

**ሰው መሆን**

የዓለም ሀገራት በቀይ ባህርና በባህረ ሰላጤው (Gulf of Aden) ላይ ያላቸው ፍላጎት ከምንግዜውም በላይ እየጨመረ መጥቷል። ኃያላን ሀገራት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚረዳቸውን ሰርጥ ለመቆጣጠር የማይፈነቅሉት ድንጋይ የማይምሱት ጉድጓድ የላቸውም። ንግድን ለመቆጣጠር፣ የሽብር ጥቃትን ለመከላከል እና በዓለም የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የፊት መስመሩን ተቆጣጥሮ ለመቆየት ደረቅ መሬት ብቻ ሳይሆን ውቅያኖሶችን በመዳፋቸው ስር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ጠንቅቀው ያውቁታል።

በዚህ ፍትጊያ ውስጥ ሁሉም የድርሻውን ለማንሳት ይራኮታል። በመሬት ላይ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት የተያዘበት በባህር ላይ ያምፃል። በዚህ የተነሳ ፍላጎቱ ከፍተኛ ውጥረት እያስከተለ ነው። ውቅያኖሶቹ በወጀቡ እየተናጡ ይገኛሉ። ከሰሞኑ በእነዚህ ቁልፍ የዓለማችን የውሃ ክፍሎች ላይ የሚደረጉ መሳሳቦች መሠረታዊ ምክንያትም ይሄው ነው።

ውቅያኖሶች አንደኛውን የዓለማችን ክፍል ከሌላኛው ጫፍ ያገናኛሉ። የንግድ መርከቦች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ቁሶችን ጭነው ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ወጀብ ጋር እየተፋተጉ ሳምንታት፣ ወራትን ጉዞ ያደርጋሉ። የሰው ልጅ መሠረታዊ ፍላጎት የሚሟላው በባህር ላይ የንግድ መስመሮች ሰላም ላይ ተመስርቶ ነው። መንግሥታት የዜጎቻቸውን ደህንነት፣ ሉዓላዊነት፣ ለማረጋገጥ የግዴታ እነዚህን የባህር ክፍሎች መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ በሳምንታት ጉዞ የሚጠናቀቀው የባህር ላይ ትራንስፖርት ሌላ አቅጣጫ ሲቀይር የወራት ጊዜን ሊፈልግ ይችላል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ነው የጂኦ ፖለቲካ ፍጥጫ የሚከሰተው። ይህ ጉዳይ ግልፅ እንዲሆንልን እንዲሁም የኢትዮጵያ የባህር በር ፍላጎት በምን ምክንያት የህልውና ጉዳይ እንደሆነ ከጉዳዩ ጋር እንደሚገናኝ ለመረዳት እንድንችል የሰሞኑን ሰው ሰራሽ የቀይ ባህር ወጀብ ጥሩ ማሳያ ነው። እስቲ እንደሚከተለው ይህንን ትኩሳት በዝርዝር ለመመልከት እንሞክር።

**የሁቲ ጥቃት ሰሞነኛው ቀውስ**

በቀይ ባህር ላይ የተነሳው ወጀብ የዓለም መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት የሳበ ነው። የዓለም ኃያል ሀገራት እና ግዙፍ መርከቦቻቸውን አቅጣጫ ያስቀየረ ትኩሳት ነው። ወጀቡ የተፈጥሮ ሳይሆን ሰው ሰራሽ ነው። አማፂያን የንግድና ወታደራዊ የባህር መስመሮችን በማወክ፣ የጣሉትን ክልከላ የተላለፈውን ደግሞ በሚሳኤል፣ በድሮንና በቀጥታ የባህር አጥቂዎች አማካኝነት ጥቃት በመሰንዘር ፍላጎቶቻቸውን ለማስፈፀም እየሞከሩ ነው። ከዚህ መነሻ የዓለም ትልቁ የባህር የንግድ መስመር የሆነው ቀይ ባህር የግጭት ቀጣና ከሆነ ሰነባብቷል። መርከቦች በየመን ሁቱ አማፂያን የድሮንና የሚሳኤል ሰለባ እየሆኑ ነው።

የግጭቱ መነሻ የእስራኤልና የጋዛ ጦርነት ሲሆን ወገንተኝነታቸውን ለፍልስጤሙ ሀማስ ያደረጉት ሁቱዎች ‹‹ከእስራኤል ጋር ግንኙነት አላቸው›› ያሏቸውን የንግድ መርከቦች ኢላማ እያደረጉ ይገኛሉ። ይህ ደግሞ የንግድ መስመሮችን የበለጠ ለአደጋ ያጋለጠ፣ የኢኮኖሚ ቀውስ እያስከተለ የሚገኝ ጉዳይ ነው። ወትሮውንም በዩክሬን-ሩሲያ ጦርነት እና በባህር ላይ ወንበዴዎች (Pirates) እየተፈተነ የነበረው የቀይ ባህር መስመር አሁን ደግሞ ዓለም አቀፍ ቅርፅ በያዘ አጀንዳ መናወጥ ጀምሯል።

አጀንዳው የእስራኤል፣ የምእራባውያንና በፍልስጤም ወገን የተሰለፉ ሀገራት ቢሆንም ከጉዳዩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ትናንሽ ሀገራትም ጭምር ሰለባ እየሆኑ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ‹‹አያገባኝም አሊያም ከደሙ ንፁህ ነኝ›› ብሎ እጅን ታጥቦና አጣጥፎ መቀመጥ አይቻልም። እንኳን በቀይ ባህር አፍንጫ ስር እየኖሩ ይቅርና ከሌላኛው የዓለም ክፍል ሆኖም በዚህ አጀንዳ ላይ ማፈግፈግ አላዋቂነትም የዋህነትም ነው።

**ተፅእኖው ምን ያህል ነው**

በዓለም ላይ በብዛት ከተጨናነቁ የመርከብ መስመሮች አንዱ የሆነው ቀይ ባህር የሚገኘው ከስዊዝ ቦይ በስተደቡብ ሲሆን አውሮፓን ከእስያና ከምሥራቅ አፍሪካ ጋር የሚያገናኘው ዋነኛ የውሃ መንገድ ነው። በደቡባዊ ጫፍ ላይ በጅቡቲና በየመን መካከል 20 ኪሎ ሜትር ያህል ስፋት ያለው ጠባብ የውሃ ጠለል ይገኛል። የየመን የሁቲ አማጽያን ያነጣጠሩበት አካባቢ ባብ ኤል-ማንዴብ የባህር ወሽመጥን ነው። አማፅያኑ የፖለቲካ ፍላጎቶቻችንን ያሳካልናል ያሉትን ክፍል ይቆጣጠሩ እንጂ በተለያየ ጊዜያት ሌሎች የባህር ላይ ወንበዴዎች ልዩ ልዩ የቀይ ባህር ክፍሎችን ኢላማቸው ሲያደርጉ ቆይተዋል።

መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከዓለም አቀፉ የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ 12 በመቶ የሚሆኑት በቀይ ባህር ያልፋል። ይህ የዓለም አቀፉ ኮንቴይነር ትራፊክ የሚይዘውን 30 በመቶውን ጨምሮ ነው። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ በየዓመቱ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚገመት የንግድ ሸቀጥና ቁሳቁስ በቀይ ባህር ውስጥ ያልፋል።

ለዚህ ነው መሰል የንግድ መስመሩን የሚያውኩ ቀውሶች ሲፈጠሩ የነዳጅ ዋጋ፣ በኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችና በሌሎች የዓለም ንግድ ዘርፎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል የሚል ስጋት የሚያይለው። ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን በሁቲዎች ጥቃት ምክንያት የተስተጓጎለውን የንግድ እንቅስቃሴ በመረጃ አስደግፈን ስንመለከት ነው።

ለምሳሌ ያህል መርስክ፣ ሃፓግ-ሎይድን እና ኤም ኤስ ሲን የተባሉ ታዋቂ የመርከብ ኩባንያዎች የተከሰተውን ቀውስ ተከትሎ ባለፈው ሳምንት ቀይ ባህርን ላለመጠቀም ወስነዋል። የአትላንቲክ ካውንስል የተባለ አንድ የምርምር ተቋም ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መረጃ በገበያ ድርሻቸው ከፍተኛ ከሆኑት አስር ትልልቅ የመርከብ ኩባንያዎች መካከል ሰባቱ በቀይ ባህር ውስጥ የሚተላለፉ እንቅስቃሴዎችን ዘግተዋል።

አንዳንድ መርከቦች በደቡባዊው የአፍሪካ ጫፍ ላይ በምትገኘው ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ አካባቢ እየተዘዋወሩ የጉዞ ጊዜያቸውን እስከ ሁለት ሳምንት ከፍ በማድረግ ላይ ናቸው። በኃይል አቅርቦት ላይ ታዋቂ የሆነው እና በነዳጅ አቅርቦት ላይ የሚሰራው ቢፒ የተሰኘው ትልቁ ካምፓኒ ሰኞ እለት በቀይ ባህር በኩል የሚያስተላልፈውን የነዳጅና የጋዝ ጭነት በሙሉ ማቆሙን ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

ከሰሞኑ በቀይ ባህር ጠለል ላይ የተከሰተው ኮሽታ ምን ያክል የዓለማችንን ኢኮኖሚ እንደሚያናጋው ማሳያ ነው። በቅርቡ በያላኑ ትኩረት ያገኘው የሁቲዎች ጥቃት መጠነ ሰፊ ተፅእኖ ስላለው እንጂ በየጊዜው በባህር ላይ የሚከሰቱ ውንብድናዎች አሉ። መርከቦች ይዘረፋሉ፣ የጉዞ ባለሙያዎች እና ካፒቴኖች ይታገታሉ። በጥቅሉ ሰው ሰራሽ ወጀቡ በሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ክትትል ካልተደረገበት የጥቃቱ ዓላማና መጠን እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ነው።

**የኢትዮጵያ ፍላጎት ከሰሞኑ ትኩሳት አንፃር**

ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ ላይ እንደመገኘቷ ይህ ጉዳይ በተዘዋዋሪ ሳይሆን በቀጥታ ይመለከታታል። ጎረቤት የሚነደው እሳት ሰደድ ሆኖ ሌላውን እንደሚያቃጥል ሁሉ በቀይ ባህር ላይ የሚከሰት ማንኛውም ቀውስ ቀድሞ ወላፈኑ ኢትዮጵያ ላይ መድረሱ የማይቀር ነው። በዚህ ምክንያት የንግድ፣ የሰላምና የትብብር ጉዳዮች ላይ ዋነኛ ተዋናይ የመሆን ፍላጎት ቢኖራት አያስደንቅም።

**ኢትዮጵያ** አብዛኛውን መሰረታዊ ሸቀጣ ሸቀጥ ፍላጎት በቀይ ባህር በኩል ከውጪ ታስገባለች። በርካታ የሀገር ውስጥ ምርቶችንም በዚሁ በኩል በማስወጣት ትነግዳለች

ኢትዮጵያ አብዛኛውን መሰረታዊ ሸቀጣ ሸቀጥ ፍላጎት በቀይ ባህር በኩል ከውጪ ታስገባለች። በርካታ የሀገር ውስጥ ምርቶችንም በዚሁ በኩል በማስወጣት ትነግዳለች። በዚህ ምክንያት በመስመሩ ላይ የሚከሰት ውንብድና አሊያም የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም የሚደረግ ጥቃት ቀጥተኛ ተጋላጭ ነች። ይህንን ጥቃት ለመከላከል ከራሷ ከባለቤቷ (ከኢትዮጵያ) በላይ ማንም አይኖርም።

ባለፉት ወራት ኢትዮጵያ የባህር በር ይገባኛል ጥያቄን ስታነሳ በምክንያትነት ከተጠቀሱ አጀንዳዎች መካከል ይሄው የደህንነት ጉዳይ አንዱ ነው። በቀይ ባህር አፍንጫ ስር ሆና እያለ በአካባቢው የሚከሰት ቀውስን ‹‹ጆሮ ዳባ ልበስ›› ብሎ ሊታለፍ የሚችል አይደለም። ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን እንዲሁም የንግድ መስመሩ ላይ ያላትን ድርሻ እየገነባች ባለችው የባህር ኃይል የመከላከል ህጋዊ መብት አላት። ለቀጣናው ሰላም መሆን እንዲሁ በትብብር የድርሻዋን ማበርከት ይኖርባታል። የሰሞኑ የሁቲ ጥቃቶችና በቀይ ባህር ላይ እየተከሰተ ያለው ሽኩቻም ይህንን እውነት የበለጠ ግልፅ አድርጎታል።

በቀይ ባህር ላይ እየተከሰተ ያለው ቀውስ ኢትዮጵያን በዲፕሎማሲያዊ መንገድ የባህር በር የማግኘት ጥያቄ የበለጠ ምክንያታዊ የሚያደርግ ነው። ይህ አመክንዮ መሬት ላይ ያለ እውነታ በመሆኑና ወቅታዊ አጀንዳ ስለሆነም ጭምር መንግሥት ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ሥራዎችን ሊያከናውንበት ይገባዋል።

የኢትዮጵያ ወደፊት መምጣት ከባቢውን ከዚህ መሰል ጥቃት አሊያም የባህር ላይ ውንብድና ለመታደግ ሁነኛ ምርጫ እንደሚሆን ማሳየት ተገቢ ነው። የሀገሪቱን የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴ ልክ እንደሌሎቹ ሀገራት ሁሉ በዚያው በቀይ ባህር ላይ ሆኖ ለመቆጣጠር ህጋዊ መብት እንዳለን ጭምር ማሳየት ተገቢ ነው።

ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ላይ ሽብርተኝነትን ስትዋጋ ነበር። ለዚህ ማሳያው በሰላም ማስከበር ተልዕኮ የፊት መስመር ተዋናይ መሆኗ ነው። የሶማሊያው አልሸባብ ከመስፋፋት እና በየጊዜው ሊያደርሰው ከሚያስበው መጠነ ሰፊ ጥቃት የተገታው በኢትዮጵያ ጠንካራ መልሶ ማጥቃትና ተሳትፎ እንደሆነ ሊዘነጋ አይገባም።

ሽብርተኛ ቡድኖች ዓላማቸውን ለማሳካት ደግሞ ድንበሮችን ብቻ አይደለም ጥሰው የሚገቡት። ይልቁኑም የጥቃት አድማሳቸውን ከየብስ በተጨማሪ በባህር ላይ ውንብድናም እያስፋፉ የንግድ መስመሮችን እያወኩ ይገኛሉ። ይህ አዲስ ስልት ሳይሆን መሬት የነካ ሃቅ ነው። ለእነዚህ አማፅያንና ሽብርተኞች ደግሞ ቀይ ባህር ቁልፍ ወሽመጥ ነው።

ቀይ ባህር በዓለም ላይ ከፍተኛ ጉዞ ከሚደረግባቸው የውሃ አካላት አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህ ምክንያት በዓለም አቀፍ ደረጃ በጣም ወሳኝ የሆነ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እንዲኖረው አስችሎታል። ጠባቡ የቀይ ባህር ርዝመቱ 2ሺህ 250 ኪሎ ሜትር እርዝመት እና 355 ኪሎ ሜትር ስፋት አለው።

በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ መካከል የሚገኘው ቀይ ባህር ከህንድ ውቅያኖስ ወደ ደቡብ፣ ከስዊዝ ቦይና ከሜድትራኒያን ባህር ወደ ሰሜን አቅጣጫ ስለሚያገናኝ ከአውሮፓ ወደ እስያ በሚወስደው አጭር የባህር መንገድ ላይ ቁልፍ ወሽመጥ ነው። በጥቅሉ በዚህ ወሳኝ ስፍራ ውስጥ (ሊያውም በአፍንጫው ስር ተቀምጦ) ድርሻን ሳይዙ መቀመጥ እንደ ግዙፍ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ውድቀት ሊታይ ይገባል። ከሰሞኑ የተፈጠረው ወጀብም የኢትዮጵያን የባህር በር ፍላጎት ይበልጡኑ ግልፅ አድርጎታል የምንለው ከዚሁ መነሻ ነው። ሰላም!!

# ዓለም አቀፍ



## ዩክሬን የጦር መሣሪያ እጥረት እንዳጋጠማት ፕሬዚዳንት ዘሌንስኪ ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሊድሚር ዘሌንስኪ ሀገራቸው ከሩሲያ ጋር እያደረገችው ባለው ጦርነት የጦር መሣሪያ እጥረት እንዳጋጠማት አስታውቀዋል።

ፕሬዚዳንት ቮሊድሚር ዘሌንስኪ በጀርመን በተካሄደ ኮንፈረንስ ላይ ባደረጉት ንግግር «ዩክሬንን ያጋጠማት የጦር መሣሪያ እጥረት ሰው ሠራሽ ነው» ብለዋል።

እንዲህ ዓይነቱ የጦር መሣሪያ እጥረት ሩሲያ እንድታሸንፍ ዕድል የሚሰጥ መሆኑንም ነው ፕሬዚዳንቱ ያስታወቁት።

ፕሬዚዳንት ዘሌንስኪ በአውሮፓ ውስጥ ያለውን «አስከፊ» ሁኔታን ለማስወገድ ተጨማሪ የጦር መሣሪያዎች በአስቸኳይ እንዲቀርብላቸውም ጥሪ አቅርበዋል።

በጦር ግንባር ያሉ የዩክሬን ወታደሮች ትጥቅ እያለቀባቸው ነው የተባለ ሲሆን፤ ይህ ያጋጠመውም በአሜሪካ ኮንግረስ ያሉ የትራምፕ ደጋፊዎች ለዩክሬን እንዲደርስ የቀረበውን የመሣሪያ ድጋፍ ማዕቀፍ በመያዛቸው ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞም ፕሬዚዳንት ዘሌንስኪ፤ «ዶናልድ ትራምፕ ወደ ዩክሬን ከመጣ አብሬው ወደ ጦር ግባር በመሄድ ላስጎበኘው ዝግጁ ነኝ» ብለዋል።

ይህም «ትክክለኛው ጦርነት በኢንስታግራም ላይ ሳይሆን ትክክለኛው ጦርነት በዩክሬን ውስጥ እንደሆነ ለማሳየት ነው» ሲሉም ዘሌንስኪ ተናግረዋል።

ከትጥቅ እጥረት ጋር ተያይዞ የዩክሬን ወታደሮች ከአቭዲቭካ ከተማ ሙሉ በሙሉ ለቀው እንዲወጡ መደረጉ ይታወሳል።

የሀገሪቱ ጦር አዛዥ አሌክሳንደር ሲርይስኪ በሩሲያ ጦር ከበባ ውስጥ ከመግባት ለመዳን ውሳኔውን ማሳለፋቸውን ተናግረዋል ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

## ጃፓን
## የዓለም ኢኮኖሚ ደረጃዋን በጀርመን ተነጠቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ጃፓን የዓለም ኢኮኖሚ ደረጃዋን በጀርመን ተነጠቀች፡፡

ላለፉት አስርት ዓመታት ከቻይና በመቀጠል የዓለማችን ሦስተኛ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት የነበረችው ጃፓን ደረጃዋን በጀርመን ተነጥቃለች፡፡

ጃፓን በ2023 ዓመት ዓመታዊ እድገቷ 4 ነጥብ 2 ትሪሊዮን ዶላር የነበረ ሲሆን የጀርመን ደግሞ 4 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ዶላር መሆኑን ተከትሎ የደረጃ ለውጥ አድርገዋል ተብሏል፡፡

ጃፓን በ1980ዎቹ የነበራት የኢኮኖሚ ግስጋሴ ዓለምን ኢኮኖሚ ትቆጣጠራለች ተብላ ተጠብቃ የነበረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች ኢኮኖሚዋ የታሰበውን ያህል ርቀት መጓዝ አልቻለም፡፡

ጎረቤቷ ቻይና በ1980ዎቹ በብዙ እጥፍ ያነሰ ኢኮኖሚ የነበራት ቢሆንም ዛሬ ላይ የቻይና ኢኮኖሚ ከጃፓን አራት እጥፍ የተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ከጃፓን ብዙ የተሻለ ዕድል የሌላት ጀርመንም ከ2027 ጀምሮ ደረጃዋን በሕንድ ልትነጠቅ እንደምትችል የአይኤምኤፍ ትንበያ ያስረዳል፡፡

የሕዝብ ቁጥር ማሽቆልቆል፣ የዋጋ ግሽበት፣ የየን ምንዛሬ በዶላር እና በቻይናው ዩዋን መበለጥ እና የዓለም ኢኮኖሚ መለዋወጥ ለጃፓን ኢኮኖሚ መጎዳት ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ሮይተርስ ዘግቧል፡፡

የጃፓን ኢኮኖሚ ምርቶችን ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ ላይ የተመሠረተ ሲሆን ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ሲልኩ የሀገሪቱ መገበያያ ገንዘብ የን መርከሱን ተከትሎ የቻይና እና ሕንድ ኩባንያዎች የገበያ ብልጫ ወስደውባታልም ተብሏል፡፡

ጃፓን ኢኮኖሚዋን ለመታደግ የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ ካልቻለች ኢኮኖሚዋ የባሰ እየተጎዳ ሊሄድ እንደሚችልም ተሰግቷል፡፡

የአውሮፓ ባለግዙፍ ኢኮኖሚዋ ጀርመንም የኢኮኖሚ እድገቷ አጥጋቢ እንዳልሆነ የተገለጸ ሲሆን የሠራተኞች እጥረት፣ የኃይል ዋጋ መናር እና የአውሮፓ ኅብረት የጣላቸው የግብር ሕጎች ኢኮኖሚዋን እየጎዱባት ነውም ተብሏል፡፡

# ስፖርት





## ጉዳፍ ፀጋይ የ5ሺ ሜትር ክብረወሰንን ዳግም ለማሻሻል አቅዳለች

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያዊቷ የ10ሺ ሜትር የዓለም ቻምፒዮን እንዲሁም የ5ሺ ሜትር ክብረወሰን ባለቤቷ ድንቅ አትሌት ጉዳፍ ጸጋይ ለተጨማሪ ክብረወሰን እየሠራች መሆኗን አስታውቃለች:: 5ሺ ሜትርን ከ14 ደቂቃ በታች በማጠናቀቅ የራሷንና የዓለምን ክብረወሰን ዳግም ለማሻሻል ያቀደች ሲሆን፤ ጠንካራዋ አትሌት ኢትዮጵያ በርቀቱ ያላትን የበላይነት እንደምታስቀጥልም የስፖርት ቤተሰቡ እምነት አሳድሮባታል::

ጉዳፍ ባለፈው የአትሌቲክስ ውድድር ዓመት በኬንያዊቷ አትሌት ፌይዝ ኪፕዬጎን እጅ ገብቶ ለሦስት ወራት የቆየውን የርቀቱን ፈጣን ሰዓት በአምስት ሰከንዶች በማሻሻል ክብሩ ዳግም የኢትዮጵያውያን ማድረጓ ይታወሳል:: በ5ሺ ሜትር የሴቶች ሩጫ ታሪክ ለ17 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ያለተቀናቃኝ ክብረወሰኑን እየተቀባበሉ ሲያሻሽሉት ኖረዋል:: በእነዚህ ዓመታት ሰዓቱ በሌላ ሀገር አትሌት እጅ የገባው አንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፤ ቆይታውም የጥቂት ወራት ዕድሜ ነው::

እአአ በ2006 አትሌት መሠረት ደፋር በቱርካዊቷ አትሌት ኤልቫን አቢይ ለገሰ ለሁለት ዓመታት ተይዞ የቆየውን ክብረወሰን በማይክሮ ሰከንዶች ብቻ በማሻሻል ነበር ክብሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ያመጣችው:: ጀግናዋ አትሌት በዓመቱ ደግሞ ኦስሎ ላይ በ8 ሰከንዶች የራሷን ሰዓት በማሻሻል አስደናቂ ገድል ስታስመዘግብ፤ በርቀቱ ታሪክ በተከታታይ ክብረወሰን የሰበረች ብቸኛዋ አትሌት በመሆን ነው::

በቀጣዩ ዓመት ደግሞ እዚያው ኦስሎ ላይ ሌላኛዋ ድንቅ ኢትዮጵያዊት አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ በሀገሯ ልጅ የተያዘውን ፈጣን ሰዓት በድጋሚ በማሻሻል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በርቀቱ ያላቸውን የበላይነት ማጠናከር ችላለች:: 14 ደቂቃ ከ11 ሰከንድ ከ15 ማይክሮ ሰከንዶችን ያስቆጠረው ይህ ሰዓት ለ12 ዓመታት በአንድም አትሌት ሳይደፈር ቆይቷል:: ከዓመታት በኋላ የርቀቱን ቁጥር አንድ አትሌትነት የያዘችው ደግሞ ሌላኛዋ ብርቱ አትሌት ለተሰንበት ግደይ ስትሆን፤ እአአ በ2020 ቫሌንሺያ ላይ 14:06.62 በሆነ ሰዓት በመሮጥ ሦስተኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት በመሆን ታሪክ ልታስመዘግብ ችላለች:: ይህንን ሰዓት ከኬንያዊቷ ተፎካካሪዋ እጅ ፈልቅቃ በማውጣት ዳግም ያሻሻለችው ደግሞ ጉዳፍ ጸጋይ ናት::



የዓለም ቻምፒዮና ጉዳፍ ጸጋይ ወቅታዊ አቋም በርቀቱ የቀሯትን ማይክሮ ሰከንዶች ማሻሻል ያስችላታል፤

አትሌቷ የክብረወሰኑ ባለቤት የሆነችው በቡዳፔስቱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በ10ሺ ሜትር ርቀት አስደናቂ ተጋድሎ በማድረግ የወርቅ ሜዳሊያ ካጠለቀች ከቀናት በኋላ ነው:: በቻምፒዮናው ሌላኛውን ድል ለማሳካት ባቀደችበት 5ሺ ሜትር እግሯ ላይ በደረሰው ጉዳት እንዳሰበችው መሮጥ ባትችልም ከሳምንት በኋላ አሪጎን ላይ በተካሄደው ዳይመንድ ሊግ ክብረወሰኑን 14:00.21 በሆነ ሰዓት ልትሰብር ችላለች:: ይህንን ሰዓት በማሻሻል ከ14 ደቂቃ በታች መግባት ደግሞ የዚህ ውድድር ዓመት እቅዷ መሆኑንም በግል የማኅበራዊ ገጿ በኩል አስታውቃለች::

በየትኛው ውድድር ሰዓቷን ለማሻሻል እንዳሰበች በግልጽ ባታሳውቅም፤ ጉዳፍ ካለችበት ወቅታዊ አቋም አንጻር ግን የቀሯትን 21 ማይክሮ ሰከንዶች በማሻሻል የርቀቱን ፈጣን ሰዓት ሌሎች እንዳይደርሱባት አድርጋ ትሰቅለዋለች ተብሎ ይጠበቃል::

በአስደናቂ ወቅታዊ አቋም ላይ የምትገኘው አትሌቷ አዲሱን የውድድር ዓመት በቤት ውስጥ የዙር ውድድር የጀመረች ሲሆን፤ የተለመደውን ስኬታማነቷን እያስመሰከረች መሆኑም ይታወቃል:: የወርቅ ደረጃ በተሰጠው የቦስተን የዙር ውድድር በ1ሺ500 ሜትር የተሳተፈችው የርቀቱን የቤት ውስጥ ክብረወሰን የሆነ ሰዓት ለማሻሻል ቢሆንም በውድድሩ የመጨረሻ ርቀት ያጋጠማት የቁርጭምጭሚት ወለምታ በጥቂት ሰከንዶች ስላዘገያት ያሰበችውን እንዳታሳካ አድርጓታል:: ሆኖም የገባችበት 3:58.11 የሆነ ሰዓት የቦስተን የቤት ውስጥ ውድድር ፈጣን በሚል ተይዞላታል::

አትሌቷ ቀጣዩ የቤት ውስጥ የዙር ውድድር መዳረሻዋ በነበረው ሌቪን ደግሞ በ3ሺ ሜትር ለፈጣን ሰዓት ብትሮጥም ክብረወሰን በማስመዝገብ ረገድ ስኬታማ ልትሆን አልቻለችም::

በምታስመዘግባቸው ነጥቦች በግላስኮው የዓለም የቤት ውስጥ ዓለም ቻምፒዮና ኢትዮጵያን በቀጥታ የመወከል ዕድል እንደሚኖራት ይታመናል:: በቻምፒዮናውም ምናልባትም በ1ሺ500 ሜትር እንዲሁም በ3ሺ ሜትር ልትሮጥ እንደምትችል ነው የሚገመተው:: የመካከለኛና ረጅም ርቀት አትሌቷ ጉዳፍ በትልልቅ የውድድር መድረኮች ባላት ተሳትፎ የተለያዩ ስኬቶችን ማስመዝገብ ችላለች:: የዚህ ዓመት ዋነኛ ግቧም የታወቀችበትን የ5ሺ ሜትር የክብረወሰን ንግሥናዋን ከማስጠበቅ ባለፈ በዓመቱ መጨረሻ በፓሪስ በሚደረገው ኦሊምፒክ የ5ሺ ሜትር እንዲሁም የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮን በመሆን የኢትዮጵያን ክብር ማስጠበቅ ይሆናል::